አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድኅረ-ምረቃ መርሀ ግብር

የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

# የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ

# በተመረጡ የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

በ

ተስፋዬ ወልደሚካኤል

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2001 ዓ.ም

# የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተመረጡ የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

አማርኛን በማስተማር (TEAM) ኤም. ኤ. ዲግሪ

በከፊል ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት

በ

ተስፋዬ ወልደሚካኤል

ሰኔ 2001

አዲስ አበባ

# የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተመረጡ የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

በ

ተስፋዬ ወልደሚካኤል

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መረሃ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት

[illegible] ---------------------------- ----------------------------

አማካሪ ፊርማ

[illegible] ---------------------------- ----------------------------

የውስጥ ፈታኝ ፊርማ

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


አጠቃሎ ........................................................................................ i

ምስጋና.......................................................................................... ii

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................ 1

1.2 የጥናቱ ዓላማ........................................................................ 2

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ................................................................... 2

1.4 የጥናቱ ገደብ ........................................................................ 2

1.5 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ትርጉም እና ልዩልዩ ምልክቶች መግለጫ ................ 3

*1.5.1 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ትርጉም ............................................. 3*

*1.5.2 የልዩ ልዩ ምልክቶች መግለጫ ................................................. 4*

ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

2.1 የንባብ ምንነት ...................................................................... 5

*2.1.1 አንብቦ የመረዳት ምንነት ........................................................ 6*

*2.1.2 የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት .................................................... 8*

2.2 አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ............................................. 10

2.3 አንብቦ የመረዳት ችሎታን መመዘን ................................................ 15

*2.3.1 አንብቦ የመረዳት ፈተና ጥያቄ ዓይነቶች ........................................ 16*

*2.3.1.1 የምርጫ ጥያቄዎች (Multiple-choice questions) ............... 16*

*2.3.1.2 ነፃ ጥያቄዎች (Open-ended questions) ............................ 17*

*2.3.2 የጥሩ አንብቦ መረዳት ፈተና ባህሪያት ........................................ 18*

2.3.3 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ ......................................... 19

ምዕራፍ ሦስት

የጥናቱ ዘዴ

3.1 የናሙናዎች አመራረጥ ............................................................. 21

*3.1.1 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ.................................................. 21*

3.1.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ........................................................21
3.1.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........................................................22
3.1.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........................................................23
3.2 የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ........................................................24
3.2.1 የጽሑፍ መጠይቅ ........................................................24
3.2.2 ምልከታ........................................................25
3.2.3 የአንብቦ መረዳት ፈተና........................................................26
ምዕራፍ አራት
የመረጃ ውጤት ትንተና
4.1 የመረጃ ውጤት ትንተና ........................................................28
4.1.1 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................................................28
4.1.2 ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................................................37
4.1.3 አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ትንተና ........................................................40
4.2 ዝርዝር ማብራሪያ ........................................................43
ምዕራፍ አምስት
5.1 ማጠቃለያ........................................................47
5.2 አስተያየት........................................................49
ዋቢዎች ........................................................50
አባሪዎች ........................................................53

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ ገጽ

1፡- አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ መለኪያ ..... 20
2፡- የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ መምህራን ..... 22
3፡- በናሙናነት የተመረጡ ትምህርት ቤቶች፣ ምድቦችና ተማሪዎች ብዛት ..... 24
4፡- መጠይቁን ሞልተው የመለሱ መምህራን በፆታ ሲመደቡ ..... 28
5፡- መጠይቁን ሞልተው የመለሱ መምህራን በትምህርት ደረጃ ሲመደቡ ..... 28
6፡- መጠይቁን ሞልተው የመለሱ መምህራን በሠለጠኑበት የትምህርት ዓይነት ሲመደቡ ..... 28
7፡- መጠይቁን ሞልተው የመለሱ መምህራን በአገልግሎት ዘመን ሲመደቡ ..... 29
8፡- በክፍሉ ውስጥ የአማርኛ ትምህርት አቀራረብ እና የመማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎች ይበልጥ የሚያተኩሩበትን በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ..... 30
9፡- መልመጃዎችን ለተማሪዎች ስለመስጠትና ስለማረም የተገኙ መረጃዎች ..... 31
10፡- የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ የንባብ ልምምድ በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..... 32
11፡- ከመማሪያ መጽሐፍ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚያዳብሩ ስለመሆናቸው የተገኙ መረጃዎች ..... 33
12፡- የተማሪዎችን የማንበብ ልምምድና ፍላጎት በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ..... 34
13፡- የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ያላቸውን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በሚመለከት የተገኘ መረጃ ..... 36
14፡- ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ስለሚከናወኑ ተግባራት የተገኙ መረጃዎች ..... 38
15፡- ምንባቡ በሚነብበት ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራትን በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ..... 39
16፡- ምንባቡ ከተነበበ በኋላ ስለሚከናወኑ ተግባራት የተገኙ መረጃዎች ..... 40
17፡- ከአራሚ አንድ (አጥኚው) የተገኘ ውጤት ..... 41
18፡- ከአራሚ ሁለት የተገኘ ውጤት ..... 41
19፡- የአራሚ ሦስት የተገኘ ውጤት ..... 42
20፡- በሦስቱ አራሚዎች የተገኘ አማካይ ውጤት ..... 42
21፡- የተጠኚዎችን ውጤት ድግግሞሽ የሚያሳይ ..... 43

## አጠቃሎ (Abstract)

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማጥናት ነው። ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በናሙናነት በተመረጡት ሦስት ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው። ሁሉንም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በጥናቱ ውስጥ ማካተትም ከአቅም በላይ ስለሆነ የተወሰኑ ተማሪዎች በናሙናነት ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዷል።

ለጥናቱ ያገለገሉት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎችን ለመምህራን የተሠራጨ የጽሑፍ መጠይቅ፣ የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ምልከታ እና አንብቦ የመረዳት ፈተና ናቸው። መምህራንን የጽሑፍ መጠይቅ በማስሞላት፣ በክፍል ውስጥ በሚሰጠው የንባብ ትምህርት ላይ ምልከታ በማካሄድ፣ ለተጠኚ ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ፈተና በመፈተን መረጃዎችን ተሰባስበዋል። የተሰበሰቡት መረጃዎችም ተተንትነዋል።

በጥናቱ የተገኘው ውጤት ጥናቱ የሚመለከታቸው ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል። ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን ከሚጠቀሱት ውስጥ ዋንኞቹ የትምህርቱ አሠጣጥና የመማሪያ መጽሐፉ በዋነኝነት ይጠቀሳሉ። በመጠይቅ በተሰበሰቡት መረጃዎች መሠረት ንባብን ከማስተማሩና ከመማሪያ መጽሐፉ አኳያ ችግሮች አሉ። በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የንባብ ትምህርት ተማሪዎችን እንደማያሳትፍ፣ አብዛኞቹ ተግባራት በመምህሩ እንደሚከናወኑ፣ ተማሪዎቹ በቂ ልምምድ እንደማያደርጉ በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል።

በመጨረሻም በዚህ ጥናት ውስጥ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ሲባል ንባብን ለማስተማር የሚደረገውን ጥረት ውጤታማ ይሆን ዘንድ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል።

# ምስጋና

ከሁሉም በላይ ይህንን ጥናት አስጀምሮ ላስፈፀመኝ ቸሩ እግዛብሔር ምስጋና ይድረሰው። በመቀጠል ከጥናቱ መባቻ ጀምሮ እስከ ፍጻሜ ድረስ ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ በየጊዜው በጥንቃቄ በማንበብ፣በማረምና ተገቢ አስተያየቶችን በመጠቆም ያላሰለሰ የሙያ ድጋፍና ምክራቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ለዶ/ር አረጋ ኃይለሚካኤል ልባዊ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እንዲሁም ዶ/ር አረጋ እንደ ጥናት አማካሪ ብቻ ሳይሆኑ እንደ ወንድምና እንደ ጓደኛ በመቅረብ ችግሬን በጥሞና ስላዳመጡኝ እና ማበረታቻቸው ስላልተለየኝ ልዩ አድናቆት አለኝ።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

አማርኛ ራሱን የቻለ ትምህርት ሆኖ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚሰጠው የተለያዩ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች ተነድፈውለት ነው፡፡ ከዓላማዎቹ ውስጥም አንዱ የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ማዳበር የሚለው ነው (ከትሚ፣1፡1984፡1 ጋር ያገናዝቧል)፡፡ የማንበብ ክሂል ከሚያካትታቸው ነጥቦች ውስጥም አንዱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር ነው፡፡ ማንበብ ያለ መረዳት ጥቅም የሌለው እንደሆነ ምሁራን (Nuttall 1982) ይገልጻሉ፡፡

በሀገራችን ውስጥ ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የተዘጋጁትን የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ስንመለከትም በውስጣቸው የሚገኙት አብዛኞቹ መልመጃዎች አንብቦ መረዳትን የሚያመለክቱ እንደሆነ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን (በየነ፣ 1985፤ ጌታቸው፣ 1996) ያስገነዝባሉ፡፡ ከመልመጃዎች ውስጥ መልመጃ አንድ በሙሉ፣ መልመጃ ሁለት በከፊል በመልመጃ ሦስት ሥር የተካተቱት ጥያቄዎች በአንብቦ መረዳት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡

በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች አንዱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር የሚመለከት ነው፡፡ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ መልመጃዎችም የሚያተኩሩት በአንብቦ መረዳት ላይ ነው ቢባልም የተማሪዎቹ አንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ ይስተዋላል፤ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መምህራንም የተማሪዎቻቸውን የአንብቦ የመረዳት ችሎታ አነስተኛ መሆኑን ሲናገሩ ይሰማል፡፡ ይሁን እንጂ እስከ ዛሬ ድረስ "የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቀተኛ ነው፣ ተማሪዎቻችን አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው፡፡" እያሉ ሐሳብ ከመሰንዘር አልፎ ጉዳዩን የእኔ ብሎ በመያዝ ጥናት አካሂዶ ከነመፍትሔው ያረጋገጠ የለም ማለት ይቻላል፡፡ ይህም በመሆኑ በእውነት እንደሚባለው የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ነውን?" መፍትሔውስ? የሚሉትን ጥያቄዎች ማንሳቱ ተገቢ ይመስላል፡፡

የዚህ ጥናት አነሳስም ተጨባጭ የሆነ ጥናት አካሂዶ እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ ነው። የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በእርግጥ አነስተኛ ከሆነም፣ የዚህ ጥናት ሌላው ዓላማ፣ የመፍትሔ ሐሳቦችን ለመሰንዘር ጭምር ነው።

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማጥናት ነው። ጥናቱም የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፤

1. የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑን ወይም አለመሆኑን መመርመር፣
2. የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ አንብቦ መረዳት ብቃት መመርመር ፣
3. የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን መመርመር።

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፤

1. የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ያስችላል፤
2. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር ያለውን ዝምድና ለመገንዘብ ያግዛል ፤
3. በሁለተኛ ደረጃ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚያስችል መሆኑን ወይም አለመሆኑን ይጠቁማል፤
4. ከጥናቱ ውጤት በመነሳት (በእርግጥ እንደሚባለው የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ አነስተኛ ከሆነ) ለችግሩ የመፍትሄ ሐሳብ ይሰነዝራል፤
5. ከአንብቦ መረዳት ጋር በተያያዘ መልኩ ወደፊት ለሚደረጉት ቀጣይ ጥናቶች የመነሻ ሐሳብ ይሰጣል።

## 1.4 የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት የሚካሄደው በአዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተመረጡ ሦስት ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ነው፤

እነርሱም አምሀ ደስታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ድል በር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ወ/ሮ ቀለም ወርቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው።

በሁለተኛ ደረጃ ከሚገኙት የክፍል ደረጃዎች ውስጥም ለጥናቱ የተመረጠው ዘጠነኛ ክፍል ነው። ዘጠነኛ ክፍል የተመረጠበት ምክንያትም በሁለተኛ ደረጃ በመጀመሪያው እርከን ላይ የሚገኝ ክፍል በመሆኑ ለጥናቱ ያመቻል ተብሎ ስለታመነበት እና ድንገት ችግር እንኳን ቢኖርበት ለችግሩ መፍትሔ ለማግኘትና ቀጣዩ ክፍል ምን መደረግ እንዳለበት ከጥናቱ ውጤት በኃላ ለማስተካከል ያመቻል ተብሎ ስለታመነበት ነው።

ከጥናቱ ስፋት የተነሳ በናሙናነት ከተመረጡት ሦስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችም በሙሉ በጥናቱ ውስጥ አልተሳተፉም

ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንጅ የማንበብ ፍጥነትን አይመለከትም። ምክንያቱም የጥናቱ ዓላማ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ብቃት መመርመር እንጂ የማንበብ ፍጥነት ማጥናት አለመሆኑ ነው። የንባብ ፍጥነት እንደየንባቡ ዓይነት ይለያያል። የንባብ ዓይነቱ ደግሞ ጽሑፉ በሚነበብበት ዓላማ (Purpose) ይወሰናል። ለምሳሌ ከአንድ ጽሑፍ ዝርዝር መረጃዎትን ለማግኘት በጥልቀት የሚያነብና የጽሑፉን አጠቃላይ መልዕክት ለመገንዘብ በገረፍ ገረፍ የሚያነብ ሰው የተለያየ የማንበብ ፍጥነት ይኖራቸዋል። ስለዚህም ጥናቱ እነዚህን ጉዳዮች ሳይመለከት በአንብቦ የመረዳት ጉዳዮች ላይ ብቻ ያነጣጠረ ነው።

## 1.5 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ትርጉም እና ልዩ ልዩ ምልክቶች መግለጫ

### *1.5.1 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ትርጉም*

ሀ. አንብቦ መረዳት (Reading comprehension):- አንድ ጽሑፍ ወይም ምንባብ የያዘውን አስፈላጊ መረጃ (Information) ሁሉ በተቻለ መጠን መገንዘብን ይመለከታል (Grellet 1981:4)። በሌላ አገላለጽ አንብቦ መረዳት ፀሐፊው በጽሑፍ ውስጥ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት (Massage) በተቻለ መጠን መገንዘብ መቻል ነው (Nuttall 1982:5፣ Williams 1993:915፣) ።

ለ. የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement test):- በአንድ በተወሰነ የክፍል ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በተወሰነ የጊዜ ገደብ በተሰጣቸው ትምህርት አማካኝነት ችሎታቸው

ከምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመለካት የሚሰጥ የፈተና ዓይነት ነው (Lewis 1985:113)።

### *1.5.2 የልዩ ልዩ ምልክቶች መግለጫ*

በዚህ ጥናት ውስጥ ከሚገኙት ልዩ ልዩ ምልክቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

| | |
|---|---|
| CF = | Cumulative frequency |
| Df = | degree of freedom |
| $\Sigma$ = | summation |
| $\Sigma x^2$= | summation of squared scores |
| F= | frequency |
| N= | number of subjects in the sample |
| P= | significance level. |
| Pr= | Correlation Cofficient of the tests |
| R= | reliability of the tests |
| Sd= | standard deviation |
| $Sd^2$= | variance |
| $Sd^2x_2$= | total variance |
| $Sd^2y_1$= | variance of test one |
| $Sd^2y_2$= | variance of test two |
| $S^2p$= | estimate variance of the population based upon the sample |
| T cal = | the calculated value of T. |
| T tab= | the tabulated value of tT in the appropriate t distribution |
| X = | scores |
| $\overline{X}$= | arthematic mean of scores |

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

### 2.1 የንባብ ምንነት

ንባብ ማለት የተጻፈን ወይም በጽሑፍ የሚገኙ ምልክቶችን የማየትና የመረዳት ሂደት ሲሆን፣ እነዚህ ምልክቶችም ተቀናጅተውና ተደራጅተው ሰፋፊ አምዶችን ይመሠርታሉ (Williams 1990፣2)። እንደ Wallace (1992፣4) አገላለጽ ደግሞ፣ ንባብ ከአንድ ጽሑፍ ጋር ተግባቦትን ለመፍጠር እንደ መተርጎሚያ መንገድ የምንገለገልበት ነው። እንዲሁም Nuttall (1982፣2) ንባብ፡-

ሀ. ፊደላትን መለየት፣ መቁጠር፣ መነጠል

ለ. ድምፅን ማፍለቅ፣ ንበት፣ መናገር፣ ወዘተ.

ሐ. አንድን ጽሑፍ መረዳት፣ ትርጉሙን መጨበጥ፣ ወዘተ.

ነው በማለት ይገልፃሉ።

በሌላ በኩል ንባብን በአንድ ቃል መግለጽ እንደማይቻል ምሁራን ይናገራሉ። ስለሆነም ንባብ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ የተለያየ ምላሽ ለመስጠት ይሞክራል። Davies (1995) "ንባብ ግላዊ ነው። ንባብ በጊዜና በቦታ ተወስኖ የሚገኝን የአንድ ጸሐፊ መልዕክት በመከተል ምላሽ ለመስጠት የምንሞክርበት አእምሮታዊ ተግባር ነው። ግላዊ ተግባር ስለሆነም የአነባበቡን ሂደትና ለጸሐፊውም የሚሰጠውን ምላሽ በቀጥታ ላናስተውለው እንችላለን" ይላሉ፤ ከዚህም ንባብ አንድ ሰው በግሉ የሚያካሂደውና አእምራዊ ተግባር መሆኑን እንረዳለን። ይህም ንባብ በተለያየ መንገድ ሊገለፅ እንደሚችል መገንዘብ አያዳግትም።

በተጨማሪም Harmer (1991፣17-18)፣ Sheng (2000) ንባብ በተቀባይ ክሂሎች ዘርፍ የሚካተት ሲሆን፣ ከምናነበው ጽሑፍ ውስጥ ቁም ነገሩን ነቅሶ ማውጣትን፣ የምንባቡን ዝርዝር ሐሳብ መረዳትን፣ አንብቦ መረጃ መቀበልንና ማስተላለፍን፣ የቃላትን ዐውዳዊ ፍች መረዳትን፣ ወዘተ. አጠቃልሎ የያዘ መሆኑን ያመለክታል። በዚህም መሠረት ንባብ በአንድ ጽሑፍ ውስጥ የቀረበን ቁም ነገር አንብቦ ለመረዳት የሚደረግን ጥረት ነው። ንባብ የአንባቢውን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ፣ ከአንድ አእምሮ ወደ ሌላው አእምሮ፣

ከጸሐፊው ወደ አንባቢው መልዕክት የሚተላለፍበት ዘዴ ነው። በዚህ ወቅትም ጥሩ የሆነ መግባባትና ግንዛቤ እንዲፈጠር ጸሐፊው፣ አንባቢውና ጽሑፉ እያንዳንዳቸው የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረክታሉ (Nuttall 1982፣18)። ይኸውም አንድ ጽሑፍ እንዲነበብ የሚያስፍራቸው ሐሳቦች አንባቢው የሚያነበውን ሐሳብ ለመረዳት ያለው የችሎታ ብቃትና ፍላጎት፣ የጽሑፍ ግልጽነት፣ የአጻጻፍ ሁኔታ፣ ወዘተ. የየራሳቸው ፋይዳ አላቸው።

Grellet (1981፣8) እንደገለፀውም፣ "ንባብ ማለት መገመት፣ መተንበይ፣ ማመሳከርና ራስን ጥያቄ መጠየቅ የሚሉትን የሚያጠቃልል ንቁ ተሳትፎ የሚያሻው ሂደት ነው።" ከዚህም ንባብ አንባቢ ከምንባቡ አውድ በመነሳት የአዳዲስ ቃላትን ፍችዎች የሚገምትበት ገና ከመነሻው ባገኘው መረጃ ላይ በመመርኮዝ የምንባቡን ዋና ይዘትና ወደፊት ምን እንደሚገጥመው የሚተነብይበት፣ የሚያነበውን ጽሑፍ መረዳትና አለመረዳቱን ራሱን ጥያቄ በመጠየቅ የሚያመሳክርበት ሂደት መሆኑን እንረዳለን። በሌላም በኩል አንባቢው የተለያዩ ምንባቦችን ሲያነብ የተለያዩ ችሎታዎችንና ስልቶችን መጠቀም እንዳለበት እንገነዘባለን።

እንደ Nuttall (2000፣4) አገላለጽ፣ ንባብ ፀሐፊው በሥራው ውስጥ ያስፈረውን ቁምነገር ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ነው። ተደራሲው በንባብ ሂደት የጽሑፉን ፍሬ ሐሳብ ለመረዳት አስፈላጊ መረጃን ከውስጥ ለይቶ ለማውጣት የጸሐፊውን ሐሳብ ይመረምራል። ስለዚህ ንባብ የሌሎችን ሐሳብ ለመረዳት እንዲሁም ለመግባባት ዓላማና ሂደት፣ ወዘተ. የምንጠቀምበት ተግባር ነው። ይህንኑ ሐሳብ David (2005፣1)ም ያጠናክሩታል።

## *2.1.1 አንብቦ የመረዳት ምንነት*

አንድን ጽሑፍ አንብቦ መረዳት ሲባል በጽሑፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት በተቻለ መጠን መገንዘብ ነው። በሌላ አባባል የሚፈለገውን መረጃ ከአንድ ጽሑፍ ውስጥ ፈልቅቆ ማውጣትን የሚይዝ ነው። አንባቢው በተገቢው ፍጥነት የሚፈለገውን መረጃ የሚያወጣበት የማይፈልገውንም እያበጠረ የሚለይበት ተራ ያልሆነ ጥልቅ ግንዛቤ የሚያመለክትበት ነው። (Smith 1985፣14 Williams 1990፣3)። እንደ Greenwood (1981፣89) አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት መገንዘብ ነው። በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ያለን መልዕክት

ለመረዳት ታዲያ የእያንዳንዱን ቃል ፍች ማወቅ የግድ አይደለም። በጽሑፍ ውስጥ በግልጽ የቀረበው መልዕክትና መልዕክቱን ለማጠናከር የገቡትን ዝርዝር ጉዳዮች መረዳት ግን አስፈላጊ ነው። ይህም ሲባል አንባቢ በግልጽ የቀረበውን መልዕክት መነሻ አድርጎ በመመርመር የሚደረስበትን ድብቅ መልዕክትም መረዳት ይጠበቅበታል። በዚህ ወቅትም በጽሑፍ ውስጥ የሚገኙትን አያያዦች አገባብ፣ አገልግሎትና ፍች መረዳት የግድ ያስፈልጋል። በተጨማሪም የምንባቡን ቅደም ተከተላዊና የሐሳብ አገላለጽና በጽሑፍ ውስጥ የተለያዩ አንቀጾች ያላቸውን የርስ በርስ ትስስር መረዳት ተገቢ ነው።

አንብቦ መረዳት የጽሑፍን ቅደም ተከተላዊ የሐሳብ አገላለጽ፣ አንዱ አረፍተ ነገር ከፊተኛውና ከተከታዩ ጋር ያለውን የሐሳብ ግንኙነትና ግጥምጥምነት የሚፈጥሩ አያያዦች የጸሐፊው ሐሳብ የሚንፀባረቅባቸው በመሆናቸው ሊተኮርባቸው የሚገቡ ናቸው (Nuttall 2000፣28)። አንብቦ መረዳት አንድ ጽሑፍ የያዘውን መረጃ መገንዘብ ነው። በእርግጥ አንብቦ የመረዳት ደረጃ ሊለያይ ይችላል። ይህም ከሚነበበው ነገር፣ ከሚነበብበት ዓላማ፣ ከአነባብ ዘዴው መለያየት ሊከሰት ይችላል። ለምሳሌ በአንድ ሰሌዳ ላይ የተለጠፈ ማስታወቂያና በአንድ መጽሔት ላይ ያልታተመ ሳይንሳዊ ጥናት በተመሳሳይ መንገድ አይነበቡም። የማስታወቂያው ፍሬ ነገር በገረፍታ ንባብ ሊደረስበት ቢቻል የሳይንሳዊ ጥናቱን ቁም ነገር ለመረዳት ግን ትኩረት ያልተለየው ጥልቅ ንባብ ያስፈልጋል (Grellet 1981፣3-4)።

አንብቦ መረዳት ማለት ፍች ማግኘት ማለት ነው። አንብቦ መረዳት የሚለው ቀጥተኛ ፍች በአንድ ላይ ማያያዝ ማለት ነው። አንብቦ መረዳት ጸሐፊው በሕትመት ላይ ያዋላቸውን ፍች-አዘል ምልክቶች በአእምሮ ውስጥ ማያያዝና ማሰላሰል ሊሆን ይችላል። በሌላም በኩል ማንኛውም ዓላማ ያለው አንባቢ የሚያከናውነው ከምንባቡ ፍችን፣ ሐሳብንና መረጃን ማግኘትና ማውጣትን ያካትታል።

በሌላ በኩል Smith (1985፣24)፣ አንብቦ መረዳት አንባቢ ይዞት ለሚነሳው ጥያቄ መልስ ማግኘት ማለት ነው። የሚነበብን ጽሑፍ አስመልክቶ ጥያቄ መጠየቅ አንብቦ የመረዳት ትምህርት ባሕሪ ነው። አንባቢ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ አገኘ ማለት በአንባቢውና በጸሐፊው መካከል ተግባቦት መኖሩን ያሳያል። በጽሑፍና በአንባቢው መካከል ተግባቦት አለ ማለት የሚቻለውም መረዳት ሲኖር ነው። ስለሆነም አንብቦ ለመረዳትንና ተግባቦትን መለያየት አይቻልም ማለት ነው። ባጭሩ አንብቦ መረዳት

ማለት ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የሚፈለገው መረጃ ለይቶ ማውጣት መቻል ነው ልንለው እንችላለን፡፡

አንብቦ መረዳት በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ እንደ Grellet (1981፣5) እና Sheng (2000፣13-15) አገላለጽ አንደኛው በምንባቡ ውስጥ በግልጽ የሰፈሩ ጉዳዮችን መገንዘብ ነው፡፡ በስሩም በጽሁፍ ውስጥ የቀረቡትን ዋና ዋና ሐሳቦች መገንዘብ፣ በግልጽ የሚታዩ ሁኔታዎችን፣ ክስተቶችን፣ ድርጊቶችን ወዘተ ቅደም ተከተል ማስታወስ፣ ግልጽ የሆኑ አንድነቶችንና ልዩነቶች መለየት፣ የምክንያትና የውጤት መሰናክል ማስታወስ ወዘተ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎቹ ተጠይቃዊ እውቀትንና ግምትን በመጠቀም በጽሁፉ ውሰጥ በግልጽ ያልሰፈሩሐሳቦችን አንብበው የሚረዱበትን ሁኔታ ይመለከታል፡፡

ይህም ካሉት መረጃዎች በመነሳት የምንባቡን ጭብጥ መለየት፣ ደጋፊ ሐሳቦችን ለይቶ ማወቅ፣ ከምክንያትና ከውጤት ጥብቅ ትስስር የተነሳ ቀጣዩን ነገር መገመት፣ በምንባቡ ውስጥ በይፋ የሰፈረን ፍንጭ በመጠቀም የገጸ-ባህሪያትን ባህሪ መገንዘብና የደራሲውን የቋንቋ አጠቃቀም መረዳትን ያካትታል፡፡

እስከ አሁን ከቀረቡት ሐሳቦች መረዳት እንደሚቻለው አንብቦ መረዳ በአንድ ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ከመገንዘብ ባሻገር ጠቃሚና አዳዲስ መረጃዎችን ለቅሞ ለማውጣት የሚያስችል ሂደትና የማንፈልገውን ደግሞ የምንተውበትን ሁኔታ ያጠቃልላል፡፡

## *2.1.2 የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት*

ንባብ የሰው ልጅ በጊዜና በቦታ ርቀት ምክንያት ሊያጣቸው የነበሩትን ነገሮች እንዲያገኝ በማድረግ ከፍተኛ አገልግት ከሚሰጡት የመገናኛና የመግባቢያ ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡ ንባብ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ያለውን ሥፍራ ተስፋዬ (1981፣60)፣ "ማንበብ በተለይ ባሁኑ በሠለጠነው ዘመን አስፈላጊ ከሚባሉት መለያዎች ውስጥ የሚደመር ነው፡፡ ማንበብ ዕውቀት የማግኛ መንገድ ብቻ ሳይሆን እንደ ዋና፣ ኳስ ጨዋታ፣ ሽርሽርና እንደ አደን ሁሉ መዝናኛ ሆነዋል" በማለት ይገልጻሉ፡፡ አንባብያን ካሉት የመረጃ ምንጮች መካከል እንደፍላጉታቸው እየመረጡ ንባብን ለየራሳቸው ጥቅም ሊያውሉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በዓለም ላይ ከሚፈጠሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችና ዕውቀቶች ጋር ለመተዋወቅና ራስን ለማዝናናት፣ በዓለም ላይ ያሉ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ

ክስተቶችን ለማወቅ፣ ወዘተ. ንባብ ከፍተኛ አገልግሎት አለው። የንባብ ትምህርት የተማሪውን የንባብ ችሎታ ለማዳበር፣ አንብቦ ጠቃሚና የማይጠቅመውን ለይቶ እንዲረዳና የሥነ ጽሑፍ ችሎታውን ለማሳደግ፣ ታሪክ እንዲያውቅ፣ ለጠቅላላ ዕውቀት፣ አእምሯዊ ብቃት ለማጐልበት፣ ወዘተ. የመሳሰሉ በርካታ ጥቅሞች አሉት (Bright 1981፣52)። ሰዎች አንድን ጽሑፍ የሚያነቡት አንድ የሚጠቅም ነገር፣ መረጃ ወይም ደስታ ለማግኘት ነው። በመጀመሪያ ዓላማዬ ብለው ያቀዱትንና ያሰቡትን ነገር ለማግኘት ሲሉ ያነባሉ (Nuttall 1982፣3)። እንደ Grellet (1981፣6) ከሆነ ደግሞ፣ የንባብ ዓላማ እንደሚከተለው ይቀርባል፤

ሀ. ለደስታ፣

ለ. ለሕይወት ወይም ለመኖር፣ እና

ሐ. ለመማር፣

ያስፈልጋል በማለት አስፍረዋል። ከዚህም ንባብ የሰዎችን ሕይወት ለመምራት አላማ ተነድፎለት ሊከናወን የሚገባ አስፈላጊ ተግባር መሆኑን እንረዳለን።

አንድን ጽሑፍ አንብቦ መልዕክቱን የመረዳት ችሎታን ለማዳበር፣ በማንበብ አጠቃላይ ዕውቀትን ለመገብየት፣ ከተለያዩ የንባብ ባሕሪያት ጋር ለመተዋወቅና ሂሳዊ የንባብ ችሎታን ለማጐልበት የንባብ ትምህርት አስፈላጊ ነው (Williams 1990፣19 እና Grant 1990፣60)። በሌላም በኩል የንባብ ትምህርት ተማሪዎች ንባብን እንዲማሩ፣ አንብበው ተፈላጊ መረጃን ማውጣት እንዲችሉ፣ ለመዝናናት ሲሉ እንዲያነቡ ለማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ በመግለጽ Harris (1990፣95-96) ቀጥለው እነዚህን ጉዳዮች ተግባራዊ ለማድረግ የንባብ ትምህርቱ ሦስት የንባብ ዓይነቶችንና ተግባራትን ማጠቃለል እንዳለበት በማስመልከት የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዩች አቅርበዋል፤

1. አገልግሎታዊ ንባብ፦ ይህ ደግሞ መረጃዎችን ማውጣት ዋና ዓላማቸው ያደረጉ ንባቦችን ሁሉ ይመለከታል፤
2. እድገታዊ ንባብ፦ ይህ ዓይነቱ ንባብ የንባብ ክሂሎችንና ስልቶችን ለማዳበር የሚያስችሉ ተግባራትን የሚያካትት ነው፤
3. የመዝናኛ ንባብ፦ መዝናናትን፣ ደስታ መጐናጸፍንና መደነቅን ዋና ዓላማዎቻቸው የሚያደርጉ ተግባራትን የሚያካትት ንባብ ነው። የተግባራቱ

ዓላማ የንባብ ዝንባሌ ለማሳየት፣ የንባብ ዝንባሌን ለማዳበርና ለማሻሻል ወይም ሥነ ጽሑፋዊ ሂስን ለማጐልበት ሊሆን ይችላል።

ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ የሚያነቡት ተፈላጊ መረጃን ለማግኘት፣ ለመደሰት ወይም ለመዝናናት፣ ወዘተ. ሊሆን ይችላል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግም ቀደም ሲል የተጠቀሱትን የንባብ ዓይነቶችና ተግባራት ተጣቃሽ ሲሆኑ የንባብ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት አያዳግትም።

የንባብን ትምህርት አስፈላጊነት አስመልክቶ McDonough and Shaw (1993፣102-103) እንደሚከተለው ያቀርባሉ፤

- በጋዜጦች፣ በመጽሔቶች፣ በዘገባዎች የሚቀርቡትን ሐሳቦች ለመረዳትና ለመዝናናት ወይም ለመደሰት፣
- መረጃ ለማግኘት፣
- ከጓደኞቻችን ጋር ሐሳብ ለመለዋወጥ፣
- አንድ ነገር መቼና የት እየተከናወነ እንደሆነ ለማወቅ፣
- መመሪያዎችን ተቀብሎ (በሥራችን ወይም በእለት ተእለት ሕይወታችን ውስጥ) ለመተግበር፣ የሚሉ ናቸው።

የንባብ ትምህርት የራሱ ግብና ስልት ያለው ሲሆን፣ ራሳቸውን ችለው፣ አቀላጥፈው ማንበብና መረዳት የሚችሉ ተማሪዎችን ለማፍራት በጣም አስፈላጊ መሆኑ እሙን ነው (Ur 1996፣150)። ንባብ የአንድን ሕብረተሰብ ዳራዊ ሁኔታ ወይም መሰረት፣ የሌሎችን ዓለማት ሰዎች የአኗኗር ዘዴና ባህል ለማወቅ ይረዳል። ንባብ ለትምህርት ብቻ ሳይሆን፣ በሕይወታችን ለምንዕፈው ማንኛውም ተግባር መረጃ በመስጠት ጠቃሚ ሚና ይጫወታል።

## 2.2 አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ

የንባብ ትምህርት ተማሪውን ውጤታማና ራሱን የቻለ አንባቢ እንዲሆን ለማድረግ በሚያግዝበት መንገድና የንባብ ስልቶችን በሚያዳብርበት መልክ መቅረብ አለበት። ውጤታማ ንባብ የሥነ ልቦናዊ ሥነ ልሳንን የንባብ ፅንሰ ሐሳብ መሠረት ማድረግ አለበት። ንባብ የሥነ ልቦናዊ ሥነ ልሳን የመተንበይ ሂደት ነው። የንባብ ሂደትም

በቋንቋና በእሳቤ መካከል ያለ የመገመት፣ የመምረጥ፣ የመመዘን፣ የማዋሐድና የመተርጎም ዑደታዊ ሂደት ነው በማለት Mei-Yun (1997፣180) ያብራራሉ።

ይህን የሥነ ልቦናዊ ሥነ ልሳን የንባብ ግንዛቤ መሠረት በማድረግ የንባብን ትምህርት አቀራረብ ውጤታማ ለማድረግ እንደሚቻል ይታመናል። ምክንያቱም ጥሩ አንባቢ ለንባብ ከቀረበለት ጽሑፍ በመነሣት የጽሑፉን ይዘት የመገመት፣ በንባብ ሂደት ያገኘውን ሐሳብ የመመዘንና ከግምቱ ጋር በማዋሐድ የምንባቡን አጠቃላይ ፍሬ ሐሳብ የመረዳት ባሕሪይ ስላለው ግንዛቤውን መሠረት ማድረግ ለትምህርት አቀራረብ የጥሩ አንባቢን ባሕርይ ለማላበስ ያስችላል።

የውጤታማ ንባብ ዓላማ ጥሩ አንባቢ የሚጠቀምባቸውን የማንበብ ስልቶችና ንዑሳን ክሂሎችን መጠቀም የሚችል ውጤታማ አንባቢ ተማሪ ለማፍራት ስለሆነ፣ Mei-Yun፥ (1997) የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚያግዝ የትምህርት አቀራረብ ባሕሪያት ማለትም በምክንያት ማንበብ፣ የመገመት፣ ስልትን መጠቀም፣ ያለፈ ዕውቀትን ለግንዛቤ ማከልና በንኡሳን ክሂሎች የመጠቀም ችሎታን መርህ ሊያደርግ ይገባዋል። ስለዚህም ተማሪዎችን ውጤታማ አንባቢ እንዲሆኑ ለማገዝ፣ የትምህርቱን አቀራረብ በመስተጋብራዊ የንባብ ግንዛቤ ላይ መመሥረት የተሻለ ነው።

በመስተጋብራዊ የንባብ ሂደት፣ ማንበብ የቃላት ፍችና ሰዋስዋዊ ሥርዓትን ማወቅ ብቻ የሚጠይቅ ሳይሆን፣ ለንባብ ከቀረበው ጽሑፍ ጋር መስተጋብር መፍጠርንም ይጠይቃል (Papalia 1987)። ተማሪው ለንባብ ከቀረበለት ጽሑፍ ጋር መስተጋብር መፍጠር አንብቦ የመረዳት ችሎታውን እንዲያዳብር፣ በቀደምት ዕውቀቱ የመጠቀም ችሎታውንና የመተንበይ ክሂሉን እንዲያጎላብት ማገዝ ያስፈልጋል። ለዚህም ተገቢ የሆነ የቅድመ ንባብ ክንዋኔዎችን በማዘጋጀት ተማሪውን ማሳተፍ ይገባል (Johnson 1982)። ይህን የንባብ ግንዛቤ መሠረት አድርጎ የሚቀርብ አንብቦ የመረዳት ትምህርት የሚያተኩረው ግንዛቤን ለማዳበር በሚደረግ የንባብ ሂደት ላይ እንጂ ምን ያህል እንደተገነዘቡ በማወቅ በውጤት ላይ ማተኮር አይደለም (Greenwood 1981፣53)። ለመረዳት የሚደረግ የንባብ ሂደት የሚጠይቀውን የንባብ ስልት ለማዳበር የሚያግዝ ወቅታዊ የሆነና ተቀባይነት ያለው የትምህርት አቀራረብ የቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜ፣ እና የድኅረ ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ የትምህርት አቀራረብ እንደሆነ በመስኩ ምሁራን እንደሚከተለው ይገልጻል፤

### ሀ. ቅድመ ንባብ (Pre-reading)

ቅድመ ንባብ አቀራረብ ተማሪዎች አንድ የቀረበን ጽሑፍ ማንበብ ከመጀመራቸው በፊት የሚከናወኑትን ተግባራት የሚያካትት ሲሆን ይህም ሁለት ዓቢይ ዓላማዎች አሉት፡፡ እነሱም ተማሪዎች ምንባቡን የሚያነቡበትን ምክንያት በመግለጽ የማንበብ ፍላጐታቸውን ማነሳሳት እና ስለ ምንባቡ ይዘት መነሻ ሐሳብ (ፍንጭ) እንዲኖራቸው ማስቻል ናቸው (Getachew 1996፣13)፡፡ በዚህ ቅድመ ንባብ ወቅት ተማሪዎች ምንባቡን የሚያነቡበት ዓላማ ሲገለጽላቸው ይገባል፡፡ ይህም ምንባቡን ምን ያህል ጠለቅ ብለው ማንበብ እንደሚገባቸው ለመወሰን ያግዛቸዋል፡፡

ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ስለምንባቡ ይዘተ ነገርና ምንነት መጠነኛ ግንዛቤና አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ የምንባቡ ይዘተ ነገር ምን ሲሆን እንደሚችል ተማሪዎች ስለ ርዕሱ ቀድሞ ካላቸው ዕውቀት በመነሳት አንዳንድ ሐሳቦች ቢሰነዝሩ ምንባቡን በሚያነቡበት ጊዜ ፍጹም አስቸጋሪ መስሎ አይታያቸውም (Statman1981:232)፡፡ ይህም ተማሪዎች ጽሑፉን ወደማንበቡ ተግባር ከመሸጋገራቸው በፊት ከርዕሱ በመነሳት ሐሳብ እንዲሰነዝሩ በማነሳሳት፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ ወዘተ. ይከናወናል፡፡

በቅድመ ንባብ ወቅት ከሚከናወኑት ተግባራት መካከል ሌላው ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላትን ፍችዎች እንዲረዱ ማድረግ እንደ ሆነ ምሁራን (ለምሳሌ Nuttall 1982:157) ይጠቁማሉ፡፡ ምንባቡን አንብቦ ለመረዳት እንቅፋት ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ አዳዲስ ቃላት ፍችዎች ለተማሪዎች በዚህ የቅድመ ንባብ ወቅት ቢቀርቡላቸው ምንባቡን አንብበው ለመረዳት ያግዛቸዋል፡፡

በሌላም በኩል የቅድመ ንባብ ደረጃ ክንዋኔዎች ተማሪዎች ምን እንደሚያነቡ ማስተዋወቂያና ለቀጣዩ ደረጃ (የንባብ ጊዜ) ተግባራትን ማስተዋወቂያ ነው McDonugh and Shaw (2003፣95) በዚህ ወቅትም መምህራን በቅድሚያ የምንባቡን ርዕስ ለተማሪዎች ያስተዋውቃሉ፣ ቀጥለውም፡-

- ለንባብ በቀረበው ርዕስ ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ የሚጠይቁ መነሻ ጥያቄዎች በማቅረብ ቀደምት ዕውቀታቸውን ከምንባቡ ይዘት ጋር እንዲያስተሳስሩ ያነቃቋቸዋል፣

- ተማሪዎቹ ምንባቡን ለምን እንደሚያነቡ በማስተዋወቅ የማንበብ ፍላጎታቸውን ያነቃቃሉ፣ ያወያያሉ፣
- የምንባቡ ይዘት ስለምን ጉዳይ ሊሆን እንደሚችል እንዲገምቱ ያደርጋሉ፣
- የንባብ ሂደትን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ቁልፍ ቃላትንና ሐረጋትን በማቅረብ ያወያያሉ።

በአጠቃላይ የቅድመ ንባብ ዋና ዓላማ ከዋናው የንባባ ሂደት በፊት የተማሪዎቹን የማንበብ ፍላጎት ለማነቃቃት የክፍል ደረጃቸውንና እድሜያቸውን ከግምት ያስገቡ የንባብ ትምህርት ይዘቶችን በመጠቀም ተማሪዎቹ እንዲሳተፉና ለእለቱ ትምህርት ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ማገገ ነው። የቅድመ ንባብ ክንዋኔዎችና ጥያቄዎች ዋና ትኩረት ግን ልጆቹ የሚያነቡትን ምንባብ በጥሩ ሁኔታ እንዲረዱና ፍላጎታቸው እንዲነቃቃ ለማድረግ ነው።

### ለ - <u>በንባብ ጊዜ (While- reading)</u>

ይህ ደረጃ ተማሪዎች ጽሑፉን የሚያነቡበት የንባብ ሂደቱ ዋነኛ አካል ነው። ይህ ባለ ሦስት ደረጃ የንባብ ትምህርት ተማሪ-መራሽ (student-centered) በመሆኑ አብዛኞቹ ተግባራት የሚከናወኑት በተማሪዎች ነው። የመምህሩ ሚናም ለተማሪዎቹ እርዳታ በመስጠት የማንበብ ሂደቱን ማፋጠን ነው (Getachew 1996:15)።

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ምንባቡን ማንበብ ያለባቸው በፀጥታ ነው ወይስ ድምፅን ከፍ በማድረግ የሚለው ጥያቄ በተለያዩ ምሁራን ይነሳል። ብዙዎቹ ምሁራን (Greenwood 1981:81-82፤ Lewis 1985:11፤ Nuttall፣ 1982) እንደሚሉት፣ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች ለትምህርት የሚቀርበውን ምንባብ በፀጥታ ቢያነቡ ይመረጣል ምሁራኑ እንደሚገልፁት ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ ምናልባት ድምፅን ከፍ አድርጎ የሚያነበው ተማሪ የአነባበብ ስልት ጥሩ ካልሆነ ሌሎቹ ተማሪዎችም ይህን ጥሩ ያልሆነ ያነባበብ ስልት ልምዱን ሊቀስሙ ይችላሉ።

በሌላ በኩል ማንበብ በባሕርይ ግላዊ ተግባር ነው ማለት ይቻላል (Molla 1987:5)። ተማሪዎችም ንባብን የሚማሩት የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው መረዳት እንዲችሉ እንጂ ሰው ሲያነብ አዳምጠው እንዲገነዘቡ ወይም ለሌላ ሰው እንዲያነቡ አይደለም። ከዚህ ባሻገርም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ

"አሁን ምን አሳሳት ይሆን?" እያሉ ይጨነቃሉ። ይህም ስጋት የሚያነቡትን ምንባብ መረዳታቸውን ሊቀንሰው ይችላል።

ይሁን እንጂ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብ አርባናቢስ ነው፤ ሙሉ በሙሉም መዘንጋት አለበት ማለት እንዳልሆነ ከላይ የተጠቀሱት ፀሐፍት ይጠቁማሉ። እንደ አስፈላጊነቱ አልፎ አልፎ በተለይም የተማሪውን የአነባበብ ስልት ለመገምገም ሲባል ተግባራዊ ይሆናል።

### ሐ. ድኅረ ንባብ (Post- reading)

በዚህ ወቅት ተማሪዎች የአነበቡትን ምንባብ የበለጠ እንዲገነዘቡት የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ። በዚህ ደረጃ ከሚከናወኑት ተግባራት ውስጥ ስለተገነበበው ምንባብ የተለያዩ ጥያቄዎችን ማቅረብና በተማሪዎች እንዲመለሱና ውይይትም እንዲካሄድባቸው ማድረግ ዋነኛው ዓላማ ነው።

የእነዚህ ጥያቄዎች ዋና ትኩረትና ዓላማም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር ነው (Nuttall 1982፣ Greenwood 1981፣83) ስለሆነም ንባብን በማስተማሩ ሂደት አንድ ምንባብ ከተነበበ በኋላ ለተማሪዎች የሚቀርቡት ጥያቄዎች አንብቦ መረዳትን የሚያዳብሩ እንዲሆኑ በጥንቃቄ መዘጋጀት አለባቸው።

በሌላም በኩል Lindsay (2006፣74-81)። በድኅረ ንባብ ደረጃ የመምህራን ተግባር ምን መሆን እንዳለበት እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤

- ምንባቡ የሚገልጸውን ሐሳብ መረዳት መቻላቸውን ለማወቅ የሚረዱ ጥያቄዎችን ያቀርባሉ፣
- ምንባቡን እንዲገመግሙ ያበረታታሉ፣
- የምንባቡ ሐሳብ ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያዛምዱ የሚረዱ ክንዋኔዎችን ያቀርባሉ፣
- ምንባቡን መነሻ በማድረግ ድርሰት እንዲፅፉ፣ ንግግር እንዲያዘጋጁ፣ በቃልም ሆነ በጽሑፍ ሪፖርት እንዲያቀርቡ የሚጋብዙ ተግባራት ይቀርባሉ። ለዚህም ደግሞ የተዘጋጀው አንብቦ የመረዳት ትምህርት አመች ሆኖ መገኘት አለበት።

በድኅረ ንባብ ደረጃ ተማሪዎች በቡድን ወይም በጥንድ ሆነው ባነበቡት ጽሑፍ ላይ በጥልቀት ሲወያዩና ሲከራከሩ ይችላሉ። Celce-Murcia (1991፣204) በድኅረ ንባብ ደረጃ በእለቱ ለንባብ የቀረበው ጽሑፍና ዋና ዋና ሐሳቦች የሚከለሱበት ክፍል ነው። እንደዚሁም በጊዜ ንባብ ደረጃ ከቀረበው ትምህርት ተነሥተው የተወሰኑ አዳዲስና ተያያዥነት ያላቸውን ቁም ነገሮች በማካተት በክፍል ውስጥና እቤታቸው ሰፋ ያለ ልምምድ የሚያከናውኑበት ደረጃ ነው። በተጨማሪም ይህ ክፍል ተማሪዎቹ ካነበቡት ምንባብ የተገነዘቡትን በራሳቸው አገላለፅ ለጓደኞቻቸው የሚያቀርቡበትና እርስ በርሳቸው እየተጋገዙ ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት ነው።

እንዲሁም የድኅረ ንባብ ደረጃ ተማሪዎች በየግላቸው የተሰጣቸውን ጽሑፍ በዝምታ ካነበቡ በኋላ በተናጠል፣ በጥንድ ወይ በቡድን ሆነው ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማነቃቃት ይቻላል። ጥያቄዎችን በኅብረት ወይም በቡድን መሥራቱ ደግሞ የበለጠ ጥሩ ይሆናል። ምክንያቱም ይህ ዓይነቱ አካሄድ እያንዳንዱ ተማሪ የመለሰውን መልስ ለምን እንደመረጠው የማስረዳት እድል ይሰጠዋል። ይህ እድል በመኖሩም ተማሪው በኅብረት ስለሚወያይ አንድ ምንባብ አንብቦ ምን ያህል እንደተረዳ ጥያቄዎቹን በሚሰራበት ወቅትም የት ላይ፣ እንዴት እንደተሳሳተ ሊያውቅ ይችላል (Nuttall 2000)።

የንባብ ትምህርቱን ከዚህ በላይ በቀረቡት ሦስት ደረጃዎች ከፍሎ ማቅረብ ትምህርቱን የበለጠ ውጤታማ ሊያደርግ ይችላል ቢባልም በየክፈለ ጊዜው የሚቀርበው የንባብ ትምህርት ሁልጊዜ በዚህ መልክ ይሰጥ ማለት አስቸጋሪ ነው (Getachew 1996)። ከዚህ በተጨማሪም የንባብ ትምህርቱ ከሌሎቹ ክሂሎች ጋር ተጣምሮ እንጂ ለብቻው ይሰጣል ማለት አይደለም።

## 2.3 አንብቦ የመረዳት ችሎታን መመዘን

በአንድ የተወሰነ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን የሚያገለግለው ዋና መሳሪያ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና እንደሆነ ምሁራን (Madson 1983: Weir 1990: Davey 1987: Stavans 1993) ይገልጻሉ። እስከ ዛሬ ድረስ በእነዚህና በሌሎችም ምሁራን አመለካከት አንብቦ የመረዳት ችሎታን በተመለከተ በተካሄዱ አያሌ ጥናቶች ውስጥ በዐቢይ መሣሪያነት ያስገለገለው አንብቦ የመረዳት ፈተና

ነው፡፡ ስለሆነም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት በሚዘጋጁ ፈተና ውስጥ የሚካተቱ ዋና ዋና የጥያቄ ዓይነቶች ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባሉ፤

## 2.3.1 አንብቦ የመረዳት ፈተና ጥያቄ ዓይነቶች

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት በሚዘጋጁ ፈተናዎች ውስጥ የሚካተቱ የተለያዩ የጥያቄ ዓይነቶች ቢኖሩም ዋና ዋና የሚባሉት "የምርጫ ጥያቄዎች እና ነፃ ጥያቄዎች" እንደሆኑ ምሁራን (Weir 1990:43፣ Madson 1983:76፣ Davery 1987:179፣ Stavans 1993:481) ይገልጻሉ፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመመዘን በተካሄዱ ጥናቶች ካገለገሉት ፈተናዎች አብዛኛዎቹ የተዘጋጁት በምርጫ እና ነጻ ጥያቄ ዓይነቶች እንደሆኑ ፀሐፊቱ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎም እነዚህን የፈተና ጥያቄ ዓይነቶች አንድ በአንድ ለመዳሰስ ይሞከራል፤

### 2.3.1.1 የምርጫ ጥያቄዎች (Multiple-choice questions)

የምርጫ ጥያቄዎች የሚባሉት ተፈታኙ የሚመልሳቸው ሲሆኑ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሚሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ ምርጫዎችም ሦስት፣ አራት ወይም አምስት ሊሆኑ ይችላሉ (Weir 1990፣43-44፣ Williams 1984፣67-68፣ Madson 1983፣ 48-49)::

የምርጫ ጥያቄዎች የራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጐኖች እንዳላቸው ባለሙያዎቹ ይጠቁማሉ፡፡ ከጠንካራና ደካማ ጐኖቻቸው ውስጥም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

<u>ሀ. ጠንካራ ጐናቸው</u>

1. በብዙዎቹ ተፈታኞች የተለመዱ በመሆናቸው ከአሰራራቸው አንጻር ግልጽ ናቸው፤
2. ጥያቄዎቹን ለመመለስ ምንባቡን አንብቦ ከመረዳት ውጭ ሐሳብን በጽሑፍ ወይም በንግግር የመግለጽ ችሎታን አይጠይቁም፤
3. አርሞ ውጤት ከመስጠት አንጻር አስተማማኝ እና ቀላል ጊዜንና ገንዘብንም ቆጣቢ ናቸው፤
4. ለሙከራ ያህል በቅድመ ፈተና መልክ በመስጠት የክብደታቸውን ደረጃ፣ የአዘጋጃጀት ድክመታቸውንም ለመገምገም አመች ናቸው፡፡

ለ. ደካማ- ጐኖቻቸው

1. ለማዘጋጀት ጥንቃቄን ይሻሉ፤ ችሎታን ይጠይቃሉ፤ ጊዜንም ይወስዳሉ ፤

2. ተፈታኞች የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች ምንባቡን ሳይረዱ በግምት ሊያገኙዋቸው ይችላሉ፤

3. ተፈታኞቹ የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች ሊያጧቸው የሚችሉት ምንባቡን ባለ መገንዘባቸው ብቻ ሳይሆን ጥያቄዎቹን ባለመረዳታቸውም ምክንያቶች ሊሆን ይችላል።

## 2.3.1.2 ነፃ ጥያቄዎች (Open-ended questions)

እነዚህ የጥያቄ ዓይነቶች በተነበበው ጽሑፍ መሠረት በጽሑፍ ወይም በቃል የሚመለሱ ሲሆኑ እንደ ምርጫ ጥያቄዎች ሁሉ የራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጐኖች አሏቸው።

ሀ. ጠንካራ ጐኖቻቸው

1. አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመመዘን የበለጠ አስማማኝ ናቸው፤

2. ከአንድ ምንባብ ብዙ ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት ያስችላሉ፤

3. ተፈታኞቹ ጥያቄዎቹ የተመሠረቱበትን ጽሑፍ አንብበው ካልተረዱ በስተቀር የጥያቄዎችን ትክክለኛ መልሶች በግምት ሊያገኛቸው አይችሉም፤

4. መጠየቅን፣ መመርመርን፣ ቅደም ተከተላዊ አገላለጽንና መረዳትን፣ ወዘተ. በተሻለ ሁኔታ ለመመዘን ያግዛሉ።

ለ. ደካማ ጐኖቻቸው

1. ከአንብቦ መረዳት አልፎ ሐሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታን ይጠይቃሉ፤

2. አርሞ ውጤት ከመስጠት አንጻር አስተማማኝነታቸው ዝቅተኛ ነው።

በአጠቃላይ የምርጫም ሆነ ነጻ የአንብቦ መረዳት የፈተና ጥያቄዎች የየራሳቸው ጠንካራ ጐኖች ያሏቸውን ያህል ደካማ ጐኖችም እንዳሏቸው ከዚህ በላይ ለመቃኘት ተሞክሯል። ከዚሀ ቀጥሎም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የሚዘጋጅ ፈተና በየትኛው የጥያቄ

ዓይነት ላይ ቢመሠረት ይሻላል? ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ባለሙያዎች የሰጡትን አስተያየቶች መሠረት በማድረግ ለመቃኘት ይሞክራል። የምርጫ ጥያቄዎች አንድን ምንባብ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመመዘን እንደማያስችሉ Brenda (1993:493) በመጥቀስ ያስገነዝባሉ። እንደነዚህ ምሁራን አመለካከት የምርጫ ጥያቄዎች ምንባቡን አንብቦ በመረዳቱ ላይ ተጨማሪም ሸክም ይፈጥራሉ። ጥያቄዎቹን ከነምርጫቸው አንብቦ መረዳቱ እንዲሁም ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥ ትክክለኛ መልሶችን ከአሳሳቾቹ (distracters) መካከል መምረጡ ለተፈታኙ አስቸጋሪ ሊሆንበት ይችላል። ይህም በፈተና ውጤቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል። ስለሆነም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት ከምርጫ ጥያቄዎች ይልቅ ነጻ ጥያቄዎች ተመራጭነት አላቸው።

ይህም የዚህን ጥናት አቅራቢ ወደ አንድ ውሳኔ አድርሶታል። የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመመዘን በሚዘጋጅ ፈተና ውስጥ በአንደኛው የጥያቄ ዓይነት ከመወሰን ይልቅ ሁለቱንም የጥያቄ ዓይነቶች ማካተት የጥናቱን ውጤት አስተማማኝ እንደሚያደርገው የጥናቱ አቅራቢ ያምናል። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የአንደኛውን የጥያቄ ዓይነት ደካማ ጎን በሌለኛውን የጥያቄ ዓይነት ጠንካራ ጎን መሸፈን ስለሚቻል ነው።

### 2.3.2 የጥሩ አንብቦ የመረዳት ፈተና ባህሪያት

የምርጫም ሆነ ነጻ አንብቦ የመረዳት የፈተና ጥያቄዎች የሚዘጋጁበት ዋነኛ ዓላማ ተፈታኞቹ የቀረበውን ምንባብ አንብበው መረዳትና አለመረዳታቸውን ለመመዘን እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጿል። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስም ምንባቦቹ ሲመረጡና ጥያቄዎቹ ሲዘጋጁ ከግንዛቤ መግባት ያለባቸው ነጥቦች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው (Hughes 1995፣119-131)፤

ሀ. በመጀመሪያ ደረጃ ጥያቄዎቹ በቀረበው ምንባብ ላይ መመሥረት አለባቸው፤ ምክንያቱም የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች ለማግኘት የግድ ምንባቡን ማንበብና መረዳት ስለሚያስፈልግ ነው። ስለዚህ በፈተናው ውስጥ ተፈታኞቹ ጥያቄዎቹ የተመሠረቱበትን ምንባብ ሳያነቡና ሳይረዱ የሚመልሷቸው ጥያቄዎችም መካተት ያለባቸውም።

ለ. በተቻለ መጠን የፈተናው ጥያቄዎች የተጻፉባቸው ቃላት፣ ሐረጋትና ዓረፍተ ነገሮች በቀጥታ ከምንባቡ የተወሰዱ ባይሆን ይመረጣል። ይህም ተፈታኞቹ ምንባቡን

ሳይረዱ ቃላቱን፣ ሐረጋቱንና ዓረፍተ ነገሮችን ለማስታወስና ከምንባቡ በማገናዘብ ብቻ የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች እንዳያገኟቸው ለመከላከል ያስችላል፡፡

ሐ. ለፈተናው የሚመረጡት ምንባቦች ለተወሰኑ ተማሪዎች የማያዳሉና የተለየ ዕውቀትን የማይጠይቁ ቢሆኑ ይበጃል (Nuttall 1982፣21)፡፡ በመሆኑም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመመዘን የሚመረጡት ወይም የሚዘጋጁት ምንባቦች ለተፈታኞች እንግዳ ማለት ከዚያ በፊት ያላነበቧቸው ቢሆኑ ጥሩ ነው፡፡ ይሁን እንጂ Hughes (1995) እንደሚሉት፣ የሚመረጡትን ምንባቦች ተፈታኞቹ ከዚያ በፊት ያነበቧቸው ወይም አያነበቧቸው ማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡

### 2.3.3 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን በዋነኛ መሣሪያነት የሚያገለግለው አንብቦ የመረዳት ፈተና እንደሆነ ቀደም ሲል በ2.3 ሥር ተገልጿል፡፡ ተፈታኞቹ በፈተናው ከሚያገኙት ውጤት በመነሳት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማወቅ ይቻላል (Nuttall 1982:37፣ Narayanaswamy 1975:144፣ Kavale 1979:27፣ Fry 1963)፡፡

Nuttall (1982:37) እንደሚገልፁት፣ የአንድን ተማሪ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተሰጠው አንብቦ የመረዳት ፈተና ካገኘው ውጤት ማወቅ ይቻላል፡፡ ተፈታኙ በፈተናው ያገኘው ውጤት 70% ከሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታው በቂ ነው ከሚባልበት ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ Narayanaswamy (1975:144) እንደሚያስገነዝቡትም፣ በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው የሚባው ተማሪ በተለመደው ፍጥነቱ በማንበብ በሚሠራው አንብቦ የመረዳት ፈተና 70% ሊያገኝ ይገባዋል፡፡ ውጤቱ ከ70% በላይ ከሆነም ጥሩ ችሎታ አለው ሊባል ይችላል፡፡ የተፈታኙ ውጤት 50% ወይም ከዚያ በታች ከሆነ ችሎታው በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

ተማሪው በተሰጠው ፈተና ያገኘው ውጤት ከ70-80 (ፐርሰንት) ከሆነ በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው፡፡ ከ50-60 ፐርሰንት ወይም ከ5-6 ከአስር ውጤት ካገኘ ችሎታው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል (Fry1963፡vii)፡፡

Kavale (1979:27) እንደሚያስገነዝቡትም፣ በአንብቦ መረዳት ፈተናው 90 ወይም ከዚያ በላይ ከመቶ ያገኘ ተማሪ ከፍተኛ የአንብቦና መረዳት ችሎታ አለው፡፡ ከመቶ 75-90 ያገኘ ተማሪ ችሎታም በቂ ከሚባልበት ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ውጤቱ ከ75% በታች ከሆነ ግን ችሎታው ዝቅተኛ ነው፡፡

በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው የሚባለው ተማሪ በሚሰጠው አንብቦ የመረዳት ፈተና ማግኘት ያለበትን ውጤት በተመለከተ Nuttall እና Narayanaswamy በተመሳሳይ ውጤት ይስማማሉ፡፡ Fry እና Kavale የሚስማሙበት ተመሳሳይ ውጤትም ቢሆን ከላይኞቹ ጋር የጎላ ልዩነት የለውም፡፡

ችሎታን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን በሰነዘሯቸው ሐሳቦች መሠረት ተማሪዎች በሚሰጣቸው አንብቦ የመረዳት ፈተና ከሚያገኙት ውጤት በመነሳት የሚያገኙትን ደረጃ እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል፤

ሠንጠረዥ 1፡- አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ መለኪያ

| ተ.ቁ | ውጤት | | ደረጃ |
|---|---|---|---|
| | ከ10 | ከ100 | |
| 1 | 10-9 | 90-100 | ከፍተኛ |
| 2 | 8-7 | 80-70 | መካከለኛ/በቂ |
| 3 | 6-5 | 60-50 | ዝቅተኛ |
| 4 | ከ4 በታች | ከ 40 በታች | በጣም ዝቅተኛ |

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በጥናቱ የተካተቱት የናሙና ትምህርት ቤቶች፣ ተጠኚ ተማሪዎች እና መጠይቅ በመሙላት የተሳተፉ መምህራን የአመራረጥ ስልት ይጠቆማል፡፡ እንዲሁም የመረጃ መሰባሰቢያ ዘዴዎችና የመረጃዎች አተናተን ስልት ይገለፃሉ፡፡

### 3.1 የናሙና አመራረጥ

#### *3.1.1 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ*

በአዲስ አበባ መስተዳድር ከሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ተጠኚዎች የሚያስተምሩበትን እና የሚማሩበትን የክፍል ደረጃ መወሰን ነው፡፡ በዚህ መሠረት በአመቺ የናሙና አመራረጥ ስልት ለዚህ ጥናት ዘጠነኛ ክፍል ተመርጧል፡፡ ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ታሳቢ ሆነዋል፡፡ አንደኛው የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ይህ ጥናት እስኪጠናቀቅ ድረስ በትምህርት ቤት አካባቢ ስለሚቆዩና አጥኚው በቂ ጊዜ ስለሚያገኝ ከሌሎቹ ክፍሎች የተሻለ አመቺነት አለው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎቹ ከአንደኛ ደረጃ አልፈው በቅርቡ ወደ ሁለተኛ ደረጃ የተመደቡ በመሆናቸው ትክክለኛውን ዕውቀታቸውን ያንፀባርቃሉ ተብሎ በመገመቱ ነው፡፡

#### *3.1.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ*

በዚህ ጥናት ውስጥ የታቀፉት ሦስት ትምህርት ቤቶች የተመረጡት በተራ እጣ የናሙና አመራረጥ (Simple random sampling) ስልት ነው፡፡ ይህ የናሙና አወሳሰድ ስልት የተመረጠበት ምክንያትም በአዲስ አበባ ውስጥ ለሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እኩል የመመረጥ ዕድል ስለሚሰጥ ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙት የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከማስተማሪያ መሣሪያዎች ዓይነት፣ ከክፍለ ጊዜ ምደባ፣ ወዘተ. አንፃር ተመሳሳይ በመሆናቸው ሁሉም እኩል የመመረጥ ዕድል እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡

የአመራረጥ ሂደቱም የሚከተለውን ይመስላል፡፡ በመጀመሪያ በአዲስ አበባ የሚገኙት አሥሩ ክፍለ ከተሞች ስሞችል ተመጣጣኝ መጠን ባላቸው ወረቀቶች ላይ ተጻፉ፡፡ ወረቀቶችም በተመሳሳይ ስልትና መጠን ከተጠቀለሉ በኋላ በአንድ ላይ ተቀላቀሉ፡፡

ከዚያም በአሥሩ ክፍለ ከተሞች አንድ የተጠቀለለ ወረቀት ብቻ በእጣ እንዲወጣ ተደረገ፡ በእጣ ከወጣው ወረቀት ላይ የተጻፈው የጉለሌ ክፍለ ከተማ በናሙናነት ተወሰደ፡፡ ከዚያም እንደገና በጉለሌ ክፍለ ከተማ የሚገኙ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስሞች በተመጣጣኝ መጠን ባላቸው ወረቀቶች ላይ ተጻፉ፡፡ ወረቀቶችም በተመሳሳይ ስልትና መጠን ከተጠቀለሉ በኋላ በአንድ ላይ ተቀላቀሉ፡፡ ከዚያም ሦስት የተጠቀለሉ ወረቀቶች ብቻ በየተራ በእጣ እንዲወጡ ተደረገ፡፡ በእጣ በወጡት ሦስት ወረቀቶች ላይ የተጻፉት አምሃ ደስታ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ድል በር አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ወ/ሮ ቀለመወርቅ ጥሩነህ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በናሙናነት ተመርጠዋል፡፡

### 3.1.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በመረጃ ማሳባሰቢያነት የተዘጋጀውን የጽሑፍ መጠይቅ (አባሪ 1ን ይመለከታል) የሞሉትን መምህራን በአዲስ አበባ ከሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሙሉ ለመምረጥ ከአቅም በላይ በመሆኑ በናሙና ከተመረጠው ክፍለ ከተማና በክፍለ ከተማው በናሙናነት ከተወሰዱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ብቻ ተመርጠዋል፡፡ በዚህም መሠረት ለጥናቱ ከተመረጡት ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን በሙሉ የተዘጋጀውን መጠይቅ እንዲሞሉ ታድሏቸዋል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡- የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ መምህራን

| ተ.ቁ | ትምህርት ቤት | የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ብዛት | | መጠይቁ የታደላቸው መምህራን ብዛት | | መጠይቁንሞልተው የመለሱት ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | ከመቶ | ቁጥር | ከመቶ | ቁጥር | ከመቶ |
| 1 | አምሃ ደስታ | 5 | 31.25 % | 5 | 31.5% | 5 | 31.5% |
| 2 | ድል በር | 5 | 31.25% | 5 | 31.25% | 5 | 31.25% |
| 3 | ወ/ሮ ቀለመወርቅ ጥሩነህ | 6 | 37.5% | 6 | 37.5% | 6 | 37.5% |
| | ድምር | 16 | 100% | 16 | 100% | 16 | 100% |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ 2 መረዳት እንደሚቻለው የጽሑፍ መጠይቁ ለሁሉም መምህራን የታደለ ሲሆን ሁሉም ሞልተው መልሰዋል፡፡

### 3.1.4 የተማሪዎች አመራረጥ

በዚህ ጥናት ውስጥ የታቀፉት የናሙና ትምህርት ቤቶች ተለይተው ከታወቁ በኃላ የሚቀጥለው ተግባር ተጠኝ ተማሪዎችን መምረጥ ነበር፡፡ በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በየምድቦቹ የተመደቡት ከችሎታቸው አንፃር አለመሆኑ ከየትምህርት ቤቶቹ በተገኘው መረጃ በመረጋገጡ ተጠኝ ተማሪዎቹን ከሁሉም ምድቦች መምረጥ የግድ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተጠኝ ተማሪዎች በሚከተለው መንገድ ከተወሰኑ ምድቦች መካከል ተመርጠዋል፡፡

1. በእያንዳንዱ በናሙናነት የተመረጠ ትምህርት ቤት ውስጥ በ9ኛ ክፍል የሚገኙ ምድቦች ብዛት ተለይተው ከታወቁ በኃላ ከጠቅላላው የምድቦች ብዛት ውስጥ ሃያ ከመቶው በተራ እጣ የናሙና አወሳሰድ (Simple random sampling) ስልት ተመረጡ፡፡ ለዚህም በመጀመሪያ በእያንዳንዱ በናሙናነት የተመረጠ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚገኙት የ9ኛ ክፍል ምድቦች በትምህርት ቤቱ የተሰጡትን መለያ ቁጥሮች ለየብቻ ተመጣጣኝ መጠን ባላቸው ወረቀቶች ላይ ተጻፉ፡፡ ከዚያም ሃያ በመቶ የሚሆኑት በእጣ እንዲወጡ ተደረገ፡፡ ለምሳሌ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ምድቦች ብዛት አምስት ቢሆን በናሙናነት የሚመረጡት ምድቦች ብዛት ሦስት (15 x 20/100=3) ይሆናል፡፡
2. በናሙናነት ከተመረጡት ከእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ ከሚገኙነት ተማሪዎች ውስጥ ሃያ ከመቶ የሚሆኑት በማይለወጥ ሥርዓታዊ የናሙና አመራረጥ ስልት (linear systematic sampling) ተመረጡ፡፡ ይህም እንደሚከተለው ተከናውኗል፡፡ በመጀመሪያ በተመረጡት ምድቦች ውስጥ የሚገኙት ተማሪዎች የስም ዝርዝር ከክፍል ኃላፊ መምህራን የስም መቆጣጠሪያ ላይ ተወሰደ፡፡ በስም መቆጣጠሪያውም ሃያ ከመቶ የሚሆኑት ተማሪዎች ብዛት ታወቀ፡፡ ለምሳሌ በምድቡ ውስጥ የሚማሩት ተማሪዎች 55 ቢሆኑ ከዚህ ምድብ የሚመረጡት ተማሪዎች አሥራ አንድ (55 x 20/1000= 11) ይሆናሉ፡፡ እነዚህ አሥራ አንድ ተማሪዎችም በስም መቆጣጠሪያ ዝርዝሩ ላይ አምስት አምስት በመዝለል (55÷ 11 = 5) የተገኙት ነበሩ፡፡ በዚህም መሠረት በስም መቆጣጠሪያው ላይ በተራ ቁጥር 1፣6፣11፣16 … 55) የተመዘገቡት ተማሪዎች ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ዘዴዎች ለጥናቱ የተመረጡት ትምህርት ቤቶች ምድቦችና የተማሪዎች ብዛት በሚከተለው ሠንጠረዥ ተመላክቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 3 በናሙናነት የተመረጡ ትምህርት ቤቶች፣ ምድቦችና ተማሪዎች ብዛት**

| ተ.ቁ | ትምህርት ቤቶች | ጠቅላላ የምድቦች ብዛት | | የናሙናነት የተመረጡት ምድቦች ብዛት ምድቦች | | በተመረጡ ምድቦች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ብዛት | | በናሙናነት የተወሰዱ ተማሪዎች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | ከመቶ | ቁጥር | ከመቶ | ቁጥር | ከመቶ | ወ | ሴ | ድምር | % |
| 1 | አምሃ ደስታ | 15 | 28.85% | 3 | 27.28% | 150 | 25% | 17 | 13 | 30 | 25% |
| 2 | ድል በር | 17 | 32.69% | 4 | 36.36% | 200 | 33.33% | 15 | 25 | 40 | 33.33% |
| 3 | ወ/ሮ ቀለመወርቅ ጥሩነህ | 20 | 38.46% | 4 | 36.36% | 250 | 41.67% | 23 | 27 | 50 | 41.67% |
| | ድምር | 52 | 100% | 11 | 100% | 600 | 100% | 55 | 65 | 120 | 100% |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ 3 መገንዘብ እንደሚቻለው በጥናቱ ከታቀፉት 600 ሦስት ትምህርት ቤቶች መካከልለ የተመረጡት ተማሪዎች 120 ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ 55 ወንዶች፣ 65 ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡

## 3.2 የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች

ለዚህ ጥናት መረጃዎችን ለማሰባሰብ በዋነኛ መሣሪያነት ያገለገሉት ዘዴዎች ሦስት ነበሩ፡፡ እነሱም 1ኛ/ መምህራን የተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ፣ 2ኛ/ የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ምልከታ፣ 3ኛ ለተማሪዎች የተሰጡ አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ናቸው፡፡ በመምህራን የተሞላ የጽሑፍ መጠይቅ፣ ከክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ምልከታ እና ለተማሪዎች ከተሰጡት አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎም እያንዳንዱን የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ለማብራራት ይሞከራል፡፡

### *3.2.1 ለመምህራን የተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ*

ለጥናቱ መረጃ ለማሰባሰብ ያገለገለው የጽሑፍ መጠይቅ በክለሳ ድርሳናቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች መሠረት በማድረግ በአጥኚው ተዘጋጅቶ በባለሙያዎች ሐሳብና አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ በናሙናነት የተመረጡት መምህራን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡

መጠይቁ ሦስት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ መረጃን (የመምህራንን ፆታና የትምህርት ደረጃ፣ የሠለጠኑበትን የትምህርት ዓይነት፣ ወዘተ.) የሚመለከቱ ጥያቄዎችን አካቷል። መምህራኑ መልሶቻቸውን በሚጽፉባቸው ባዶ ቦታዎችም በጥያቄዎቹ አንፃር ተሰጥተዋል።

የመጠየቁ የሁለተኛውና የሦስተኛው ክፍሎች ደግሞ በክፍል ውስጥ የሚካሄደውን የንባብ ልምድ፣ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ የንባብ ተሳትፎ፣ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ፣ ወዘተ. የሚመለከቱ ጥያቄዎችን አካተዋል። በክፍል ሁለት ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ ጥያቄ የየራሱ ምርጫዎች የተሰጡት ሲሆን መምህራኑም ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥ የሚስማሙበትን እንዲመርጡ ተጠይቀዋል። በክፍል ሦስት ውስጥ ለተካተቱት ጥያቄዎችና ሐሳቦች ደግሞ አንድ ዓይነት የሆኑ አምስት አምስት መመዘኛዎች ተሰጥተዋል። እነዚህ መመዘኛዎችም "በጣም ከፍተኛ"፣ "ከፍተኛ"፣ "መካከለኛ"፣ "ዝቅተኛ" እና "በጣም ዝቅተኛ" የሚሉ ናቸው። መምህራኑም ለእያንዳንዱ ጥያቄ ወይም ሐሳብ የሚስማሙበትን መመዘኛ መርጠው እንዲያመለክቱ ተገልጾላቸዋል። የመጠይቁ አራተኛ ክፍል መምህራኑ መልሶቻቸውንና አስተያየታቸውን በነጻ የሚገልፁባቸውን ጥያቄዎች ይዟል። የመጠይቁ ዓላማ በግልጽ ከተገለጸና በእያንዳንዱ ክፍል ሥር የሚገኙ ጥያቄዎችን አመላለስ በተመለከተም ግልጽ መመሪያዎች ከተጻፉበት በኋላ መምህራኑ እንዲሞሉት ተደርጓል።

### 3.2.2 የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ምልከታ

የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከሚወሰንባቸው ነጥቦች ውስጥ በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የንባብ ዋነኛው ነው (Getachew 1996)። በመሆኑም በ9ኛ ክፍል ውስጥ የንባብ ልምምድ እንዴት እንደሚካሄድ መረጃ ለማግኘት ሲባል ምልከታዎች ተካሂደዋል።

ምልከታዎቹን ለማካሄድም ፈቃደኛ መምህራንን ማግኘትና የንባብ ልምምድ የሚካሄድባቸውን ክፍለ ጊዜያት ማወቅ አስፈላጊ ነበር። ስለሆነም ከየትምህርት ቤቶቹ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን መካከል ሙሉ ፈቃደኛ የሆኑና የንባብ ልምምድ የሚካሄድባቸውን ክፍል ጊዜያት ለአጥኚው ያሳወቁ ሁለት ሁለት መምህራን ለጥናቱ ተመርጠዋል። ለመምህራኑ የምልከታው ዓላማ በሚገባ የተገለጸላቸው ሲሆን

በምልከታው ወቅትም ሁልጊዜ የሚገለገሉበትን ስልት እንዲከተሉ ማሳሰቢያ ተሰጥቷቸዋል።

ሁሉም ምልከታዎች አንድ በአንድ ለትምህርት የቀረበ ምንባብ ተጀምሮ እስከሚፈፀምበትና አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች እስከሚመለሱበት ድረስ ያለው የጊዜ ገደብ እንዲያጠቃልሉ ተደርጓል። ይህም ከአንድ እስከ ሁለት የአርባ ደቂቃ ክፍለ ጊዜያትን ፈጅቷል።

ምልከታዎቹ የተካሄዱት በክለሳ ድርሳናቱ ውስጥ በቋንቋ ትምህርት ባለሙያዎች ስለንባብ ትምህርት አሰጣጥ የተገለጸውን በመመርኮዝ በተዘጋጀ የምልከታ ዝርዝር መሣሪያነት ነው (አባሪ 2ን ያገናዝቧል)። የምልከታ ዝርዝሩ በክፍሉ ውስጥ የንባብ ትምህርት ወቅት ተግባራዊ ይሆናሉ ተብሎ የታሰቡ ዝርዝር ነጥቦችን ያካተተ ነው፣ Gage1963፣289-299)። ምልከታውን የሚያካሂዱት ባለሙያዎች መብዛት በመምህሩም ሆነ በተማሪዎች ላይ የመደናገር ስሜት ስለሚፈጥር ምልከታው በአንድ ባለሙያ ብቻ ቢካሄድ እንደሚሻል በተጠቆመው መሠረት (Gage 1963፣306) ይህኑ ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት በዚህ ጥናት ውስጥ ምልከታዎቹ የተካሄዱት በአንድ ባለሙያ ብቻ ነው። ምልከታዎቹ በሚካሄዱበት ጊዜ በምልከታ ዝርዝሩ ውስጥ የሰፈሩት ነጥቦች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ከሆኑ በየአንጻሩ በተሰጡት ቦታዎች የ "✓" ምልክት፣ ካልሆነ ደግሞ የ "x" ምልከታ ተደርጓል። ምልከታዎቹ በዚህ መልክ ተካሂደው መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ተተንትነው ቀርበዋል።

### *3.2.3 የአንብቦ መረዳት ፈተና*

#### *3.2.3.1 አዘገጃጀት*

በአንድ በተወሰነ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን የሚያስችለው ዋነኛ ዘዴ የአንብቦ መረዳት ፈተና አዘጋጅቶ መስጠት እንደሆነ ምሁራንን (Weir 1990፣ Modson 1983፣ Davey 1987፣ Stavans 1993) በመጥቀስ ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳናቱ ውስጥ ተገልጿል።

በዚህ ጥናት ውስጥ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት ሲባል ሁለት አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች (አባሪ 2 "ሀ"ን እና "ለ"ን ይመለከቷል)። በአጥኚው ተዘጋጅተው ተጠኚዎቹ እንዲፈተኗቸው ተደርጓል። ፈተናዎቹ ሁለት የሆኑበት ምክንያትም በአንድ ፈተና ላይ ብቻ ከመመሥረት ይልቅ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ

ፈተናዎችን መስጠት የጥናቱን ውጤት የበለጠ አስተማማኝ ስለሚያደርገው ነው (Harris 1965፣ Madson 1983)።

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን ከሚያገለግሉ የጥያቄ ዓይነቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ "የምርጫ" እና "ነጻ" የሚባሉት እንደሆኑ ምሁራንን (Weir 1990፣ Madson 1983፣ Stavans1993) በዋቢነት በመጥቀስ በክለሳ ድርሳናቱ ውስጥ ተገልጿል። ለዚህ ጥናት መረጃ ማሰባሰቢያነት በተዘጋጁት ሁለት ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የጥያቄ ዓይነቶችም የምርጫ እና ነጻ ጥያቄዎች ናቸው።

በእያንዳንዱ ፈተና ውስጥ አስር አስር ጥያቄዎች ተካተዋል። በሁለቱም ፈተናዎች ውስጥ የሚገኙት የምርጫ እና ነጻ ጥያቄዎች ብዛት እኩል ነው። የምርጫ ጥያቄዎች መልሶቻቸው በግምታዊ አሰራርና ለመልሶችም ፍንጭ በሚሰጡ የአዘገጃጀት ድክመቶች፥ እንዳይገኙ ጥንቃቄ ለማድረግ ተሞክሯል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት ምርጫዎች ውስጥ አሳሳቾችን ከትክክለኛ መልሶች ጋር ለማመሳሰልና እንዳይሳሳቱ ለማድረግም ተሞክሯል።

ለሁለቱ ፈተናዎች የተመረጡት ምንባቦች በተፈታኞቹ ጠቅላላና የቀድሞ ዕውቀት ላይ እንዳይመሠረቱ፣ የተለያየ ዕውቀትንም እንዳይጠይቁ ጥረት ተደርጓል። (Hughes 1995)። በአንብቦ መረዳት ፈተና ውስጥ የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች ለማግኘት ጥያቄዎቹ የተመሠረቱበትን ምንባብ ማንበብና መረዳት የግድ በመሆኑ ተፈታኞቹም ንባቦቹን ሳያነቡና ሳይረዱ ቀድሞ ባላቸው ዕውቀት ወይም ያዘገጃጀት ድክመት የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልሶች እንዳያገኟቸው ሲባል የተቻለው ሁሉ ጥንቃቄ ተደርጓል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትንና የመሳሰሉትን ነጥቦች ሁሉ ከግንዛቤ በማስገባት የተማሪዎችን ደረጃ ይመጥናሉ፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታንም ይመዝናሉ ተብለው የታመነባቸውን ፈተናዎች በአጥኚው ከተዘጋጁ በኃላ በሁለት የቋንቋ እና በሌሎች ሁለት የሥነ- አእምሮ (Psychology) ምሁራን ተገምግመውና መሻሻል ተደርጉባቸው እንደገና ተዘጋጅተዋል። እንደገና የተዘጋጁት ፈተናዎችም በባለሙያዎቹ ተገቢነት (validity) እንዳላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ውጤት ትንተና

### 4.1 የመረጃ ውጤት ትንተና

በዚህ ንዑስ ክፍል ሥር በተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ መንገዶች የተገኙ መረጃዎች እየተተነተኑ ይቀርባሉ፡፡

#### *4.1.1 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና*

ለዚህ ጥናት አንዱ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ለመምህራን የተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ እንደሆነ በ3-2-1 ተገልጿል፡፡ በዚህም መሠረት በመጠይቁ የተገኙት መረጃዎች ከዚህ ቀጥሎ ይተነተናሉ፡፡

*ሀ. በክፍል አንድ ከቀረቡ ጥያቄዎች ከተገኙ መረጃዎች*

ሠንጠረዥ 4፣ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ መምህራን በፆታ ሲመደቡ

| ተ.ቁ | ፆታ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | ሴት | 7 | 43.8 |
| 2 | ወንድ | 9 | 56.2 |
| | ድምር | 16 | 100 |

ሠንጠረዥ 5፡- መጠይቁን ሞልተው የመለሱ መምህራን በትምህርት ደረጃ ሲመደቡ

| ተ.ቁ | የትምህርት ደረጃ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | ዲፕሎማ | - | - |
| 2 | ቢ.ኤ.ዲግሪ | 14 | 87.5 |
| 3 | ኤም.ኤ.ዲግሪ | 2 | 12.5 |
| | ድምር | 16 | 100 |

ሠንጠረዥ 6፡- መጠይቁን ሞልተው የመለሱ መምህራን በሠለጠኑበት የትምህርት ዓይነት ሲመደቡ

| ተ.ቁ | የሠለጠኑበት የትምህርት ዓይነት | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | አማርኛ | 16 | 100 |
| 2 | እንግሊዝኛ | - | - |
| 3 | ሌላ | | |
| | ድምር | 16 | 100 |

ሠንጠረዥ 7፡- መጠይቁን ሞልተው የመለሱ መምህራን በአገልግሎት ዘመን ሲመደቡ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዘመን | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | ከ1-5 ዓመት | 7 | 43.7 |
| 2 | ከ6-10 ዓመት | - | |
| 3 | ከ 11-15 ዓመት | - | |
| 4 | ከ 16-20 ዓመት | 3 | 18.7 |
| 5 | ከ 21-25 ዓመት | 2 | 12.6 |
| 6 | 26-30 ዓመት | 4 | 250 |
| | ድምር | 16 | 100 |

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሠንጠረገሮች (4-7) መረዳት እንደሚቻለው፣ መጠየቁን ሞልተው ከመለሱት 16 መምህራን ውስጥ ሰባቱ (43.8) ሴቶች ሲሆኑ ዘጠኙ (56.2%) ደግሞ ወንዶች ናቸው። በትምህርት ደረጃው አንጻር ዲፕሎማ፣ ቢ.ኤ ዲግሪና ኤም.ኤ. ዲግሪ ያላቸው መምህራን ብዛት በዚሁ ቅደምተከተል መሠረት ቢ.ኤ. ዲግሪ 14(87.5%) ኤም.ኤ ዲግሪ 2(12.5%) ሲሆን ሁሉም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት የአማርኛ ቋንቋ ነው። ቋንቋውን ለማስተማር ካላቸው ልምድ አኳያ ከ1-5፣11-15፣ከ16-20፣ ከ21-25፣ ዓመታት እና ከ26 ዓመት በላይ ያገለገሉት መምህራን ብዛት እንደ ቀደምተከተሉ 7(43.7%)፣ 3(18.7%)፣ 2(12.6%) እና 4(25%) ነው።

ከዚህ በላይ የተሰጠው መረጃ መምህራኑ ከትምህርት ደረጃ፣ ከሠለጠኑበት የትምህርት ዓይነት፣ ከአገልግሎት ዘመን፣ ወዘተ. አንፃር መምህራኑ ለጥናቱ ተገቢና ጠቃሚ መረጃዎችን ሊሰጡ መቻላቸውን ነው።

*ለ. በክፍል ሁለት ከቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና*

ሠንጠረዥ 8፡- በክፍሉ ውስጥ የአማርኛ ትምህርት አቀራረብ እና የመማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎች ይበልጥ የሚያተኩሩበትን በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች

| የጥያቄው ተ.ቁ. | ጥያቄ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚከተለው ውስጥ ይበልጥ የሚያጐለብተው የትኛውን ክፍል ነው? | 7 | 43.75 |
| | ሀ. አንብቦ የመረዳት ችሎታን | 2 | 12.5 |
| | ለ. አዳምጦ የመረዳት ችሎታን | 2 | 12.5 |
| | ሐ. ሐሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታን | 5 | 31.25 |
| | መ. ሐሳብን በንግግር የመግለጽ ችሎታን | | |
| 2 | በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የሚቀርበው ትምህርት ይበልጥ የሚያተኩረው በየትኛው ክሂል ላይ ነው? | | |
| | ሀ. በማዳመጥ | 2 | 12.5 |
| | ለ. በመናገር | 6 | 43.75 |
| | ሐ. በማንበብ | 7 | 37.5 |
| | መ. በመጻፍ | 1 | 6.25 |
| 4 | በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ መልመጃዎች ከሚከተሉት ውስጥ ይበልጥ የሚያተኩሩት በየትኛው ላይ ነው? | | |
| | ሀ. አንብቦ በመረዳት | 6 | 37.5 |
| | ለ. አዳምጦ በመረዳት | 2 | 12.5 |
| | ሐ. ሐሳብን በንግግር በመግለጽ | 4 | 25 |
| | መ. ሐሳብን በጽሑፍ በመግለጽ | 4 | 25 |

ከዚህ በላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከቱት ጥያቄዎች የክፍሉ ውስጥ የአማርኛ ትምህርት አቀራረብ እና የመማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎች ይበልጥ ስለሚያተኩርበትና ስለሚያጐለብቱት የክሂል ዘርፍ መረጃ ለማግኘት የቀረቡ ናቸው። በክፍል ውስጥ የሚቀርበው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይበልጥ የሚያተኩረው በማንበብ ክሂል ላይ እንደሆነ ከመጠይቁ መላሾች አብዛኞቹ (43.75) ገልፀዋል።

የ2ኛው ጥያቄ ትምህርቱ ይበልጥ የሚያጐለብተውን በተመለከተ የቀረበ ነው። ለዚህ ጥያቄም ቢሆን ባብዛኞቹ (43.75) በተመረጠው አንብቦ የመረዳት ችሎታን የሚለው ነው።

በ4ኛው ተራ ቁጥር ላይ ለቀረበው ጥያቄ በብዛት የተሰጠው መልስ "አንብቦ በመረዳት" ላይ የሚል ነው። ይህን መልስ የሰጡትም በቁጥር 6 (37.5)ናቸው። ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው፣ በክፍል ውስጥ የሚቀርበው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይበልጥ

የሚያተኩረው በማንበብ ክሂል ላይ፣ ይበልጥ የሚያጉለብተውም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ሲሆን፣ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት መልመጃዎችም ይበልጥ የሚያተኩሩት በአንብቦ የመረዳት ላይ ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 9፡- መልመጃዎችን ለተማሪዎች ስለመስጠትና ስለማረም የተገኙ መረጃዎች**

| የጥያቄው ተ.ቁ. | ጥያቄ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 3 | ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች መልመጃዎችን ምን ያህል ይሰጣሉ? | | |
| | ሀ. ሁልጊዜ እሰጣለሁ | 7 | 43.75 |
| | ለ. አልፎ አልፎ እሰማለሁ | 3 | 18.75 |
| | ሐ. አብዛኛውን ጊዜ እስማለሁ | 6 | 37.5 |
| | መ. እንዲህ አልፈዋለሁ | - | - |
| 5 | ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ውስጥ በየጊዜው የሚሰጧቸውን መልመጃዎች የሚሰሩ ምን ያህል ናቸው? | | |
| | ሀ. ሁሉም ይሠራሉ | 2 | 12.5 |
| | ለ. ጥቂቶቹ ይሠራሉ | 4 | 25 |
| | ሐ. አብዛኞቹ ይሠራሉ | 9 | 56.25 |
| | መ. ጨርሶ አይሠሩም | 1 | 6.25 |
| 6 | ለተማሪዎች የሚሰጧቸውን መልመጃዎች ምን ያህል ተከታትለው ያርማሉ? | | |
| | ሀ. ሁልጊዜ አርማለሁ | 4 | 25 |
| | ለ. አብዛኛውን ጊዜ አርማለሁ | 8 | 50 |
| | ሐ. አልፎ አልፎ አርማለሁ | 4 | 25 |
| | መ. ጨርሶ አላርምም | 4 | 25 |

ከዚህ በላይ የቀረበው ሠንጠረዥ የአማርኛ መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው መልመጃዎችን ከመስጠትና ከማረም አኳያ ያላቸውን ልምድ የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት መምህራን ውስጥ አብዛኞቹ (43.75%) ለተማሪዎቻቸው መልመጃዎችን ሁልጊዜ እና አብዛኛውን ጊዜ እንደሚሰጡ ገልፀዋል፡፡ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸውን መልመጃዎች ተከታትለው ማረማቸውን በተመለከተም 8 የሚሆኑት (50%) ሁልጊዜ አርማለሁ እና አብዛኛውን ጊዜ አርማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡

5ኛው ጥያቄ የሚሰጧቸውን መልመጃዎች የሚሠሩት ተማሪዎች ምን ያህሉ እንደሆኑ ይጠይቃል፡፡ መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት መምህራን ውስጥ 9 (56.25%) ሁሉም ይሠራሉ "እና" አብዛኞቹ ይሠራሉ የሚል መልስ ሲሰጡ 4 ያህል የሚሆኑት (25%) ደግሞ ጥቂቶቹ ይሠራሉ በማለት መልሰዋል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ከመጠይቁ በተገኘው መረጃ መሠረት መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው መልመጃዎችን ይሰጣሉ የሰጧቸውን መልመጃዎችም ተከታትለው ያርማሉ፡፡ ይሁን እንጂ የሚሰጧቸውን መልመጃዎች የሚሰሩት ተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ይህም በተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ አይቀርም፡፡

ሠንጠረዥ 10፡- የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ የንባብ ልምምድ በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ትንተና

| የጥያቄው ተ.ቁ. | ጥያቄ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 7 | ተማሪዎች ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ የሚያደርገው | | |
| | ሀ. ሁልጊዜ ነው | 3 | 18.75 |
| | ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው | 8 | 50 |
| | ሐ. አልፎ አልፎ ነው | 5 | 31.25 |
| | መ. በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ አያደርግም | - | - |
| 8 | ተማሪዎቹ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ካሉት ምንባቦች ውጭ ሌላ ተጨማሪ ምንባቦችን የሚያነቡት | | |
| | ሀ. ሁልጊዜ ነው | - | - |
| | ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው | 3 | 18.75 |
| | ሐ. አልፎ አልፎ ነው | 9 | 56.25 |
| | መ. ተጨማሪ ምንባቦችን አያነቡም | 4 | 25 |
| 9 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በየተራ እንዲያነቡ የሚደረገው | | |
| | ሀ. ሁልጊዜ ነው | 2 | 12.5 |
| | ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው | 4 | 25 |
| | ሐ. አልፎ አልፎ ነው | 7 | 43.75 |
| | መ. ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ አይደረግም | 3 | 18.75 |
| 10 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች በየተራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ የሚያደርጉት ከሆነ በሚያነቡበት ጊዜ ቢሳሳቱ ምን እርምጃ ይወስዳሉ | | |
| | ሀ. የንባቡ ሂደቱን በማቋረጥ ስህተቱን እራሴ አስተካክዬ አነባለሁ | 2 | 12.5 |
| | ለ. መሳሳታቸውን ያላወቅሁ በመምሰል ንባባቸውን እንዲቀጥሉ አደርጋለሁ | 4 | 25 |
| | ሐ. አስተካክለው እስከሚያነቡ ድረስ የተሳሳቱትን እንዲደግሙ አደርጋለሁ | 10 | 62.5 |

በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የንባብ ልምምድና የተማሪዎች ተሳትፎ ምን እንደሚመስል መረጃ ለማግኘት ሲባል በሠንጠረዥ 10 ውስጥ ያሉት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በጥያቄ 7 እንደተመለከተው፣ ተማሪዎች ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ የሚያደርገው አብዛኛውን ጊዜ እንደሆነ የገለፁት መምህራን (50%) ናቸው ይህም ሌሎችን መልሶች ከሰጡት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ነው፡፡ በተራ ቁጥር 8

ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ካሉት ምንባቦች ውጭ ሌሎች ተጨማሪ ምንባቦችን እንዲያነቡ የሚደረገው ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ሲባል ለቀረበው ጥያቄ ብዙዎቹ (56.25%) የሰጡት መልስ አልፎ አልፎ ምንባቦችን ያነባሉ የሚል ነው።

9ኛው ጥያቄ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሁልጊዜም ይሁን አብዛኛውን ጊዜ ወይም አልፎ አልፎ በሚያነቡበት ጊዜ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ የሚያደርገው ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ የቀረበ ነው። ከመጠይቁ መላሾች ውስጥ (43.75%) አልፎ አልፎ ተማሪዎቻቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል። ጥያቄ 10 በጥያቄ 9 ላይ የተመሠረተ ነው። መጠይቁን ከሞሉት መምህራን ውስጥ (62.5%) ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለሚያነቡበት ጊዜ ሲሳሳቱ የንባብ ሂደቱን በማስቆም አስተካክለው እስኪያነቡት ድረስ የተሳሳቱትን እንዲደግሙት እንደሚያደርጉ ገልፀዋል። % ደግሞ የንባብ ሂደቱን በማስቀም ራሴ አስተካክዬ አነበዋለሁ በማለት መልሰዋል። ለጥያቄው መሳሳቸቸውን ያላወቅሁ በመምሰል ንባባቸውን እንዲቀጥሉ አደርጋለሁ በማለት የመለሱ 25% ብቻ ናቸው። ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ሲሳሳቱ በዚህ መንገድ ማስተካከልም "አሁንም ምን እሳሳት ይሆን" እያሉ እንዲጨነቁ ሊያደርጋቸው ይችላል።

### *ሐ. በክፍል ሦስት ከቀረቡት ጥያቄዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና*

ሠንጠረዥ 11፡- ከመማሪያ መጽሐፍ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚያዳብሩ ስለመሆናቸው የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ብቃት | 2 | 12.5 | 9 | 56.25 | 5 | 31.25 | | | | |
| 2 | ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የመስራት ፍላጎት ምን ያህል ነው | - | - | 8 | 50 | 3 | 18.75 | 4 | 25 | 1 | 6.25 |
| 5 | በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚጫወተው ሚና ምን ያህል ነው | 4 | 25 | 6 | 37.5 | 6 | 37.5 | | | | |

ለ1ኛው ጥያቄ "ዝቅተኛ"ና "በጣም ዝቅተኛ" የሚሉት የመረጡት የለም። ይህም የሌሎቹን ምርጫዎች ከመረጡት አንፃር ሲታይ መጠኑ ያነሰ ነው። ሆኖም ግን

በአንጻሩ 9 (56.25%) "ከፍተኛ"፣ እና (12.5%) "በጣም ከፍተኛ" እና "መካከለኛው" (31.25%) መሆኑን ገልፀዋል። በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ብቃት በተመለከተ በ2ኛው ተራ ቁጥር ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው መልስ መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ 3 (18.75%) የሚሆኑት መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን የአንብቦ መረዳት ችሎታ የማዳበር ብቃታቸው መካከለኛ እንደሆነ ገልፀዋል። እንዲሁም 8(50%) የተማሪዎቹን የአንብቦ መረዳት ችሎታ የማዳበር ብቃታቸው ከፍተኛ እንደሆነና 5 (31.25%) በጣም ዝቅተኛና ዝቅተኛ በማለት መልሰዋል።

ከዚህ በላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ምንባቦችና መልመጃዎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የማዳበር ብቃታቸው ከፍተኛ ነው። በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የማዳበር ብቃት በተጨማሪ ከፍተኛ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ሠንጠረዥ 12፡- የተማሪዎችን የማንበብ ልምምድና ፍላጐት በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ. | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | |
| | | በቁጥር | ከመቶ | በቁጥር | ከመቶ | በቁጥር | ከመቶ | በቁጥር | ከመቶ | በቁጥር | ከመቶ |
| 3 | ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? | | | 2 | 12.5 | 8 | 50 | 6 | 37.5 | | |
| 4 | ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ-ጊዜ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት የንባብ ልምምድ | | | 2 | 12.5 | 7 | 43.75 | 5 | 31.25 | 2 | 12.5 |
| 6 | ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ውስጥ በክፍል ውስጥ የማንበብ ፍላጐት ያላቸው ተማሪዎች ብዛት ምን ያህል ነው? | | | 2 | 12.5 | 10 | 62.5 | 3 | 18.75 | 1 | 6.25 |
| 7 | ተማሪዎች በአማርኛ የተጻፉ የተለያዩ ጽሑፎችን የማንበብ ፍላጐት ምን ያህል ነው ? | | | 3 | 18.75 | 8 | 50 | 5 | 31.25 | | |
| 8 | ተማሪዎች አንድን ምንባብ ከአነባቡ በኋላ የሚሰጡት ምላሽ ምን ያህል ነው? | | | 4 | 25 | 8 | 50 | 4 | 25 | | |
| 9 | ከክሂሎች አንጻር ምንባብን ለማንበብ የሚሰጡት ጊዜ ምን ያህል ነው? | 2 | 12.5 | 4 | 25 | 6 | 37.5 | 4 | 25 | | |

ሠንጠረዥ 12 የተማሪዎችን የማንበብ ልምድና ፍላጐት በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎችንና የተሰጡ መልሶችን ይዟል። በ3ኛው ጥያቄ የተሰጠው መልስ ተማሪዎች በመማሪያው መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ምንባቦች የማንበብ ፍላጐታቸውን መካከለኛ እንደሆነ መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ (43.75%) ያመላክታል፤ በተጨማሪም (43.75%) የሚሆኑት "በጣም ዝቅተኛ"፣ "ዝቅተኛ" በማለት መልዋል። "ከፍተኛ" በማለት የመለሱት (12.5%) ብቻ ናቸው።

በ4ኛው ጥያቄ የተሰጠው መልስ ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ውስጥ የሚያደርጉት የንባብ ልምምድ ከፍተኛ እንደሆነ የገለጹት 12.5% ሲሆን፣ መካከለኛ እንደሆነ የጠቆሙት ደግሞ 50% ናቸው የቀሩት 37.5% ደግሞ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ አመልክተዋል። በ5ኛው ተራ ቁጥር ለቀረበው ጥያቄ 62.5% የሚሆኑት በጣም ከፍተኛ ሲሆን 37.5% የሚሆኑት ደግሞ መካከለኛ የሚል መልስ ሰጥተዋል።

ለ6ኛው ጥያቄ የተሰጠው መልስም መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ 12.5% ከፍተኛ፣ 62.5% መካከለኛ እና 25% በጣም ዝቅተኛ፣ ዝቅተኛ በማለት መልሰዋል። ይህም በክፍል ውስጥ የማንበብ ፍላጐት ያላቸው ተማሪዎች ቁጥር መካከለኛ መሆኑን ያመለክታል።

ለ7ኛ ጥያቄ የተሰጠው መልስም መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ 50% መካከለኛ ሲሆን በጣም ዝቅተኛ ብለው የመለሱት 31.25% ብቻ ናቸው የቀረው 18.75% ከፍተኛ በማለት መልሰዋል። ይህም በአማርኛ የተጻፉ የተለያዩ ጽሑፎችን የማንበብ ፍላጐት መካከለኛ መሆኑን ይጠቁማል

8ኛው ጥያቄ ተማሪዎች አንድን ምንባብ ከአነባቡ በኃላ የሚሰጡት ምላሽ ምን ያህል እንደሆነ ያመለክታል። ለጥያቄውም 25% የሚሆኑ "ከፍተኛ" የሚሉትን ሲመርጡ 50% የሚሆኑት ደግሞ "መካከለኛ" የሚሉትን መርጠዋል ቀሪው 25% "በጣም ዝቅተኛ" የሚሉትን በመምረጥ አመልክተዋል።

9ኛው ጥያቄ ተማሪዎች በክሂሎች አንጻር ምንባብን ለማንበብ የሚሰጡት ጊዜ ምን ያህል እንደሆነ ያመለክታል መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ 37.5% "በጣም ከፍተኛ" በማለት መልሰዋል። ጥያቄውን መካከለኛ በማለት የመለሱት 37.5% ሲሆኑ፣ 25% የሚሆኑት ደግሞ "በጣም ዝቅተኛ" በማለት መልሰዋል። ለጥያቄው ከተሰጡት መልሶች መረዳት የሚቻለው የተማሪዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር ስናዛምደው የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ከፍተኛ እንደሆነ እንገነዘባለን።

ሠንጠረዥ 13፡- የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ያላቸውን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በሚመለከት የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ. | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 10 | በአጠቃላይ ሲታይ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው? | | | 3 | 18.75 | 8 | 50 | 5 | 31.25 | | |

በሠንጠረዥ 13 ውስጥ የተመለከተው ጥያቄ በአጠቃላይ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መረጃ ለማግኘት የቀረበ ነው፡፡ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን ውስጥ 50% የሚሆኑት “መካከለኛ” በማለት መልሰዋል፡፡ የቀሩት ደግሞ 31.25 “በጣም ዝቅተኛ” 18.75% ደግሞ “ከፍተኛ” በማለት መልሰዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ መረጃ መሠረትም የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ በመካከለኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

*መ. በክፍል አራት ከቀረቡት ጥያቄዎች የተገኙ መረጃዎች*

ለመምህራን ከተሰራጨው የጽሑፍ መጠይቅ በክፍል አራት ሥር የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ነው፡፡ ዝቅተኛ የሆነበትን ምክንያት፣ በመማሪያው መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ምንባቦችና መልመጃዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን የማዳበር ብቃት፣ ወዘተ. የሚያመለክቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለጥያቄዎቹ መጠይቁን ሞልተው በመለሱት መምህራን የተሰጡት መልሶችም የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

1. ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን በመምህራን ከተሰጡት ምክንያቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤
   ሀ. የተማሪዎች የዳበረ የንባብ ልምድ አለመኖር
   ለ. በሚሰጠው ትምህርት ውስጥ ከመጽሐፍ ውጭ ሌሎች ተጨማሪ ምንባቦችና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አለመካተታቸው
   ሐ. የተማሪዎች የማንበብ ልምድ ማነስ
   መ. የማንበብ ክሂልን፣ እንዲሁም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚያስችሉ መጻሕፍት አለመኖር
2. የመማሪያ መጽሐፍ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ አያዳብሩም በማለት የመለሱ መምህራን የሰጧቸው ምክንያት

ሀ. ከምንባቡ የወጡ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች መጠይቅን፣ መመራመርን፣ ወዘተ የማይጠይቁ አለመሆናቸው፣

ለ. የምንባቦችና የመልመጃዎች ከተማሪዎች ችሎታ በላይ ወይም በታች መሆናቸው፣

ሐ. በመጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ምንባቦች የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት የሚያነሳሱ አለመሆናቸው።

3. የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር በመምህራን የተሰጡ የመፍትሔ ሐሳቦች፤

ሀ. የመማሪያ መጽሐፍን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር በሚያስችል መንገድ ማዘጋጀት፣

ለ. ተማሪዎች በትርፍ ጊዜያቸው እንዲያነቡ መገፋፋት፣

ሐ. በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙት ምንባቦች በተጨማሪ ሌሎች ማራኪ፣ የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያነሳሱና ችሎታቸውንም የሚመጥኑ ምንባቦችን ለትምህርት ማቅረብ።

### 4.1.2 ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚሰጠት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ውስጥ አንዱ የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ማዳበር እንደሆነ በዚሁ ሥራ በመግቢያው ውስጥ ተገልጿል። የንባብ ክሂልን ማዳበር ከሚያካትታቸው ነጥቦች ውስጥ አንዱ ደግሞ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር ነው።

ይህንን መሠረት በማድረግም በ9ኛ ክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርቱ እንዴት እንደሚከናወን መረጃ ለማግኘት ሲባል ምልከታዎች ተካሂደዋል። ከምልከታዎቹ የተገኙት መረጃዎችም እንደሚከተለው ተተንትነዋል፤

ሠንጠረዥ 14፡- ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ስለሚከናወኑ ተግባራት የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | የመምህሩና የተማሪው ተግባራት | ድግግሞሽ ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | መምህሩ የምንባቡን ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጽፋሉ። | 3 | 75 |
| 2 | መምህሩ የምንባቡን ርዕስ ለተማሪዎች በቃል ይናገራል። | 2 | 50 |
| 3 | መምህሩ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ አዳዲስ ቃላትን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጽፋል። | 1 | 25 |
| 4 | መምህሩ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ አዳዲስ ቃላትን ፍችዎች ለተማሪዎች ይገልጻል ። | - | - |
| 5 | መምህሩ ለተማሪዎች ምንባቡን የሚያነብበትን ዓላማ ይገልጽላቸዋል። | - | - |
| 6 | ተማሪዎች ስለ ምንባቡ መልዕክት ሐሳብ ይሰነዝራል ። | - | - |

በሠንጠረዥ 14 እንደሚታየው በተራ ቁጥር 1 ፣ 2 እና 3 የሰፈሩት ነጥቦች ተግባራዊነት አዎንታዊ ነው በምልከታው ከተካተቱት መምህራን ውስጥ 75% የሚሆኑት የንባብ ሂደቱ ከመጀመር በፊት የምንባቡን ርዕስ ለተማሪዎቻቸው ሲናገሩ 50% የሚሆኑት ርዕሱን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጽፏሉ ። 25% የሚሆኑት ደግሞ የተገኙትን አዳዲስ ቃላት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጽፏሉ።

በተራ ቁጥር 4፣5እና 6 የተመለከቱት ነጥቦች ተግባራዊነት ግን ዜሮ ነው። በምልከታው የታቀፉት መምህራን በሙሉ (100%) የምንባቡ ሂደት ከመጀመሩ በፊት አዳዲስ ምንባቦች ለተማሪዎቻቸው እንደማይገልጹ ነው። ተማሪዎችም የአንዳንድ ቃላትን ፍቺዎች እንዲገምቱ አይጋብዟቸውም። እንዲሁም ምንባቡን ወደ ማንበብ ሂደት ሽግግር ከመደረጉ በፊት ተማሪዎች ስለምንባቡ ይዘት (መልዕክት) ሐሳብ እንዲሰነዝሩ ዕድል አይሰጡም። ተማሪዎቹ ምንባቡን የሚያነቡበትን ዓላማ ወይም ምንባቡን ካነበቡ በኋላ ምን እንደሚጠበቅባቸው አይገለፅላቸውም። ይህም ጽሑፉ ምን ያህል ጠለቅ ብለው ማንበብ እንዳለባቸው፣ ካነበቡ በኋላም ምን እንደሚጠበቅባቸው ለማወቅ ችግር ይፈጥርባቸዋል።

ሠንጠረዥ 15. ምንባቡ በሚነበብበት ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራትን በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | የመምህሩና የተማሪዎች ተግባራት | ድግግሞሽ ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 7 | ተማሪዎች በፀጥታ ያነባሉ፡፡ | 3 | 75 |
| 8 | መምህሩ ምንባቡን ድምፁን ከፍ አድርጐ ያለምንም ገለጻ ያነባል፡፡ | 3 | 75 |
| 9 | መምህሩ ድምፁን ከፍ አድርጐ ዕረፍተ ነገር በዓረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በአንቀጽ እያብራራ ያነባል፡፡ | 1 | 25 |
| 10 | ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ተራ በተራ ያነባሉ ፡፡ | 3 | 75 |
| 15 | ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ ሲሳሳቱ ፡፡ | 2 | 50 |
| 15.1 | መምህሩ ንባባቸው በማቋረጠ ስህተቱን አስተካክሎ ያነበዋል፡፡ | | |
| 15.2 | አንባቢው ተማሪ ማንበቡን አቋርጦ እንዲያስተካክል በመምህሩ ይነገረዋል፡፡ | 2 | 50 |
| 15.3 | ተማሪው ማንም ጣልቃ ሳይገባበት ማንበቡን ይቀጥላል፡፡ | 1 | 25 |

ሠንጠረዥ 15 አንድ ለትምህርት የሚቀርቡ ምንባብ በክፍለ ውስጥ በሚነበብበት ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራትን ያመለክታል፡፡ በተራ ቁጥር 7 እንደተገለጸው በምልከታው ከታቀፉት መምህራን ውስጥ 75% ያህሉ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች ተማሪዎች ድምፃቸውን ቀንሰው በፀጥታ ያነባሉ፡፡ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ያለ ምንም ገለፃ ያነባሉ የሚሉት ደግሞ 75% ናቸው፡፡

በተራ ቁጥር 9 እና 10 እንደተመለከተው፣ በምልከታው ከተካተቱት መምህራን መካከል 25% የሚሆኑ መምህሩ ድምፁን ከፍ አድርጐ ዓረፍተ ነገር በዓረፍተ ነገር፣ ወይም አንቀጽ በአንቀጽ እያብራራ እንደሚያነብ ሲገልጽ፣ 75% ደግሞ ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ተራ በተራ ያነባሉ፡፡

በተራ ቁጥር 15 ሥር የሰፈሩት ነጥቦች በ10ኛው ተራ ቁጥር ላይ የተመሰረቱ ሲሆን ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተራ በተራ በሚያነቡበት ጊዜ ፊደላትንና ቃላትን ከመግደፍና አሳሳቶ የማንበብ ስሕተቶች ሲፈጽሙ መምህራን የሚወስዷቸውን የማስተካከያ እርምጃዎች ለማሰስ የቀረቡ ናቸው፡፡ ተማሪዎችን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተራ በተራ ከሚያስነብቡት አራት መምህራን ውስጥ ሁለት (50%) የሚያነቡት ተማሪዎች በሚሳሳቱበት ጊዜ የንባብ ሂደቱን በማስቆም ስሕተቱን ራሳቸው

አስተካክለው ያነቡታል። ተማሪዎቹ ማንበባቸውን አቋርጠው የተሳሳቱን አስተካክለው እንዲያነቡ የሚያደርጉት ብዛትም ተመሳሳይ ሁለት (40%) ነው። በተማሪዎቹ ላይ ጣልቃ ሳይገቡ ተማሪዎቹ ማንበባቸውን እንዲቀጥሉ በፀጥታ የሚከታተሉት መምህራን አንድ (25%) ብቻ ናቸው።

**ሠንጠረዥ 16፡- ምንባቡ ከተነበበ በኃላ ስለሚከናወኑ ተግባራት የተገኙ መረጃዎች**

| ተ.ቁ | የመምህሩና የተማሪዎች ተግባራት | ድግግሞሽ | % |
|---|---|---|---|
| 11 | ተማሪዎች ስለተነበበው ምንባብ በጥንድ ወይም በቡድን እርስ በርስ ይወያያሉ። | 3 | 75 |
| 12 | መምህሩ የምንባቡን ፍሬ ሐሳብ ለተማሪዎች ይገልጻሉ። | 2 | 50 |
| 13 | መምህሩ ተማሪዎችን የራሱን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቃል። | 1 | 25 |
| 14 | ተማሪዎች ግልጽ ያልሆነላቸውን ነጥብ መምህሩን ይጠይቃሉ። | 1 | 25 |

በሠንጠረዥ 16 ውስጥ የተካተቱትን ነጥቦች መሠረት በማድረግ ለትምህርትነት የቀረበው ምንባብ ከተነበበ በኃላ የሚከናወኑ ተግባራትን ለማሰስ ተሞክሯል። በተገኘው መረጃ መሠረት በተራ ቁጥር 11 ተማሪዎች ስለተነበበው ምንባብ በጥንድ ወይም በቡድን እርስ በርስ ይወያያሉ የሚለው 75% እንዲሁም የምንባቡን ፍሬ ሐሳብ ለተማሪዎች በአጭሩ የሚገልፁት መምህራን ብዛትም 50% ነው።

በምልከታው ውስጥ ከተካተቱት መምህራን ውስጥ 25% የሚሆኑት ተማሪዎችን የራሳቸውን የቃል አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ሲጠይቁ 25% ደግሞ ተማሪዎች ግልጽ ያልሆነላቸው ጥያቄ ሲኖር መምህሩን ይጠይቃሉ።

### *4.1.3 አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ትንተና*

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማመልከት እንደሆነና ለዚህም መረጃ ለማግኘት ሲባል ሁለት የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ተዘጋጅተው ተጠኚዎቹ እንዲፈተኗቸው መደረጉ ቀደም ሲል በ3.2.3.1 ተገልጿል። ለጥናቱ የተመረጡ ተጠኚ ተማሪዎች 120 ሲሆኑ ለትንተናው የቀረበውም በዚሁ የ120 ተማሪዎች ውጤት ነው።

በሁለቱ ፈተናዎች ውስጥ የሚኙት የምርጫ ጥያቄዎች በአጥኚው ብቻ ታርመዋል። ነፃ ጥያቄዎች ደግሞ በሦስት ምሁራን (በአጥኚው፣በአንድ የአማርኛ ድኅረ ምረቃ ተማሪ

እና በአንድ የመሰናዶ የአማርኛ መምህር) ከታረሙ በኃላ፣ የሦስቱ አራሚዎች አማካይ የምርጫ ጥያቄዎች አንድ አንድ ነጥብ ሲሰጣቸው ነፃ ጥያቄዎች ደግሞ ሁለት ሁለት ነጥብ ይዘዋል። በዚህ መሠረት እያንዳንዱ ተማሪ በእያንዳንዱ ፈተና ያገኘው ውጤት ከ15 ታስቦ የሁለቱ ፈተናዎች ውጤት በአንድ ላይ ከ30 በተደመረ በኃላ ለትንታኔ ያመች ዘንድ ወደ 10 ተለውጧል። በዚህ መልክ የተገኘው የፈተና ውጤትም የሚከተለውን ይመስላል።

ሠንጠረዥ 17፡- ከአራሚ አንድ (አጥኚው) የተገኘ ውጤት

| ውጤት | ድግግሞሽ | CF |
|---|---|---|
| 10 | 3 | 3 |
| 9 | 5 | 8 |
| 8 | 6 | 14 |
| 7 | 3 | 17 |
| 6 | 3 | 20 |
| 5 | 7 | 27 |
| 4 | 20 | 47 |
| 3 | 29 | 86 |
| 2 | 23 | 109 |
| 1 | 8 | 117 |
| 0 | 3 | 120 |

የተጠኚዎቹ ብዛት = 120 አማካይ ውጤት = 4.73

የተጠኚዎች ውጤት ድምር 568 መደበኛ ልይይት = 2.01

ሠንጠረዥ 18፣ ከአራሚ ሁለት የተገኘ ውጤት

| ውጤት | ድግግሞሽ | CF |
|---|---|---|
| 10 | 2 | 2 |
| 9 | 5 | 7 |
| 8 | 7 | 14 |
| 7 | 4 | 18 |
| 6 | 2 | 20 |
| 5 | 7 | 27 |
| 4 | 21 | 48 |
| 3 | 40 | 88 |
| 2 | 22 | 110 |
| 1 | 10 | 120 |
| 0 | 0 | 120 |

የተጠኚዎች ብዛት = 120 አማካይ ውጤት = 3.78

የተጠኚዎች ውጤት ጠቅላላ ድምር = 454 መደበኛ ልይይት = 1.4

ሠንጠረዥ 19. የአራሚ ሦስት የተገኘ ውጤት

| ውጤት | ድግግሞሽ | CF |
|---|---|---|
| 10 | 3 | 3 |
| 9 | 5 | 8 |
| 8 | 6 | 14 |
| 7 | 5 | 19 |
| 6 | 4 | 23 |
| 5 | 4 | 27 |
| 4 | 19 | 46 |
| 3 | 42 | 88 |
| 2 | 21 | 109 |
| 1 | 1 | 120 |
| 0 | 0 | 120 |

የተጠኝዎች ብዛት = 120 አማካይ ውጤት = 3.80

የተጠኝዎች ውጤት ጠቅላላ ድምር = 579 መደበኛ ልይይት = 1.45

ሠንጠረዥ 20. በሦስቱ አራሚዎች የተገኘ አማካይ ውጤት

| ውጤት | ድግግሞሽ | CF |
|---|---|---|
| 10 | 3 | 3 |
| 9 | 5 | 8 |
| 8 | 6 | 14 |
| 7 | 4 | 18 |
| 6 | 5 | 23 |
| 5 | 6 | 29 |
| 4 | 20 | 49 |
| 3 | 38 | 87 |
| 2 | 22 | 109 |
| 1 | 10 | 119 |
| 0 | 1 | 120 |

በዚህ ሠንጠረዥ ከተገኘው ውጤት መረዳት የሚቻለው የተጠኝዎች ብዛት 120፣ የተጠኝዎች ውጤት ጠቅላላ ድምር 579፣ አማካይ ውጤት 3.80 እንዲሆም መደበኛ ልይይት 1.45 መሆኑ ነው።

ከዚህ በላይ ከቀረቡት የውጤት ሠንጠረገች መረዳት እንደሚቻለው በሦስቱ አራሚዎች የተገኙት የፈተና ውጤቶች በጣም ተቀራራቢ ናቸው። ለምሳሌ በአራሚ አንድ፣ በአራሚ ሁለት እና በአራሚ ሦስት የተገኙ አማካይ ውጤቶች በተከታታይ 4.73፣3.78 እና 3.80 ናቸው። ይህም ከአስተራረምና ከውጤት አሰጣጥ አንጻር በንጽጽር መልክ ሲታይ በአራሚዎቹ መካከል ከፍተኛ /የጎላ/ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል።

ሠንጠረዥ 21፡- የተጠኝዎችን ውጤት ድግግሞሽ የሚያሳይ

| ውጤት | ብዛት | % |
|---|---|---|
| 10-9 | 8 | 6.77 |
| 8-7 | 10 | 8.3 |
| 6-5 | 11 | 9.16 |
| 4-3 | 58 | 48.33 |
| 2-0 | 33 | 27.5 |

በሠንጠረዥ 21 እንደተመለከተው ከ10-9፣8፣7፣ ከ6-5፣ ከ4-3፣ እና ከ2 በታች ውጤት ያገኙት ተማሪዎች ብዛት በተከታታይ 6.7፣ 8.3፣9.16፣48.33 እና 27.5 ከመቶ ስሌት ሲታሰብ በቅደምተከተሉ መሠረት 6.7%፣ 8.3%፣9.16% 48.33% እና 27.5% ነው፡፡ ይህም የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያመለክታል፡፡

## 4.2 ዝርዝር ማብራሪያ

በመምህራን ተዘጋጅቶ ከሚሰጥ የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት በመነሳት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማወቅ እንደሚቻል የተለያዩ ምሁራን አመለካከት (Nuttall 1982፣ Narayanaswamy 1975፣ Fry 1963፣ Kavale: 1979) በማጣቀስ ተገልጿል፡፡ ምሁራኑ እንደሚሉት ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ከፍተኛ ነው የሚባለው ከ10 ከተመዘገበ ፈተና ከ10-9 ውጤት ካገኙ ነው፡፡ ችሎታቸው በቂ ነው የሚባለው ደግሞ ውጤታቸው ከ8-7 ሲሆኑ ነው፡፡ ውጤታቸው 6 እና ከዚያ በታች ከሆነ ግን ችሎታቸው "ዝቅተኛ" ወይም "በጣም ዝቅተኛ" መሆኑን ያመለክታል፡፡

ለዚህ ጥናት በተሰጡት ፈተናዎች በሦስቱ አራሚዎች የተገኘውን አማካይ ውጤት በሚያሳየው ሠንጠረዥ 21 እንደተመለከተው በጥናቱ ከታቀፉት 120 ተማሪዎች ውስጥ ከፍተኛ የሚያሰኘውን ዉጤት (10-9) ያገኙ ተማሪዎች 6.7% ብቻ ናቸው፡፡ በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታን የሚያመለክተውን ውጤት (ከ8-7) ያገኙ ተማሪዎች ብዛት 8.3% ነው፡፡ ከቀሩት ተማሪዎች ውስጥ 9.16% ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን የሚገልፀውን ውጤት (ከ6-5) አግኝተዋል፡፡ ሌሎቹ 75.83% ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ችሎታን የሚያመለክተውን ውጤት (ከ4 በታች) ያስመዘገቡ ናቸው፡፡

ስለሆነም በዚህ ጥናት የአንብቦ መረዳት የፈተና ውጤት መሠረት አብዛኞቹ (84.99%)ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ይህም የተማሪዎቻቸውን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተመለከተ መምህራኑ ከሰጡት መልስ ጋር ተመሳሳይ ነው። የተሰራጨላቸውን የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተው ከመለሱት መምህራን ውስጥ አብዛኞቹ የተማሪዎቻቸው አንብበው የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ ገልጸዋል። ሠንጠረዥ 12ን ያገናዝቧል።

በአጠቃላይ ወደ ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ስንመለስ በዚህ ጥናት ከታቀፉት ተማሪዎች ውስጥ (84.99%) የሚሆኑት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ከፍ ሲል ተገልጿል። የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከሚወስንባቸው ነጥቦች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ደግሞ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት ነው (Getachew: 1996) የአማርኛ ቋንቋ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚሰጣቸው ዓላማዎች ውስጥ አንዱ የማንበብ ክሂልን ማዳበር እንደሆነ በቋንቋው ሥርዓተ ትምህርት ላይ ተገልጾ ይገኛል። የማንበብ ክሂል ከሚያካትታቸው ውስጥ አንዱ ደግሞ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ነው። ይሁን እንጂ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለማዳበሩን ነው። ስለሆነመ ከዚህ በታች የክፍሉ ውስጥ የንባብ ትምህርት እንዴት እንደሚካሄድ ለመግለጽ ይሞክራል።

አንድ ምንባብ በክፍል ውስጥ በሚቀርብበት ጊዜ፣ ምንባቡን ወደ ማንበብ ሂደት ሽግግር ከመደረጉ በፊት ተማሪዎች ስለ ርዕሱ ቀድሞ ካላቸው እውቀት በመነሳት የምንባቡ መልዕክት ምን ሊሆን እንደሚችል ሀሳብ ሲሰነዝሩ ጽሑፉን በሚያነቡበት ጊዜ ፍፁም አዲስ መስሎ እንዳይሰማቸው ይረዳቸዋል (Williams 1984፣7፣ Nuttall 1982:154):: ከዚህ ባሻገርም በምንባቡ ውስጥ ያሉ የምንባቡ መልዕክት ለመረዳት እንቅፋት የሚሆኑ አንዳንድ አዳዲስ ቃላት ለተማሪዎቹ በቅድሚያ ሊገለፅላቸው ይገባል። (Statman 1981: 232፣ Nuttall 157):: ተማሪዎቹ ጽሑፍን የሚያነቡበትን ዓላማ መግለጽም በቅድም ንባብ ወቅት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል አንዱ እንደሆነ ምሁራን (Nuttall 153፣ Williams 1991፣7) ያስገነዝባሉ። ይህም ተማሪዎቹ ምንባቡን ምን ያህል ጠለቅ ብለው ማንበብ እንዳለባቸው ለመወሰን ይረዳቸዋል።

በዚህ ጥናት ውስጥ በተካተቱት ትምህርት ቤቶች ግን ይህ ተግባራዊ እንደማይሆን ለመምህራን ከተሰራጨው መጠይቅና በክፍል ውስጥ በተካሄደው ምልከታ ለማረጋገጥ

ተችሏል፡፡ ምልከታ ከተደረገባቸው ክፍለ ትምህርቶች ውስጥ በማንኛውም ቢሆን ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ተማሪዎቹ ካላቸው ቅድመ ዕውቀት በመነሳት ስለምንባቡ ሐሳብ እንዲሰነዝሩ ሲደረግ አልታየም፤ ምልከታ ከተካሄደባቸው መምህራን ውስጥ አብዛኞቹ ወደማንበቡ ሂደት የሚሸጋገሩበት የምንባቡን ርዕስ ለተማሪዎቹ በቃል ለመግለጽ ወይም በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ አልፈው ግን ከዚህ በላይ ጽሑፉን አንብበው ለመረዳት ተማሪዎችን ያግዛሉ የተባሉ ተግባራትን እንዲከናወኑ አያደርጉም፡፡

ብዙ ምሁራን በሚቀበሉት ባለሦስት ደረጃ የንባብ ትምህርት አቀራረብ መሠረት ለትምህርት የቀረበው ምንባብ በሚነበብበት ጊዜ መከናወን ስላለባቸው ጉዳዮችም ምሁራኑ የሚሰነዝሯቸው አስተያየቶች አሉ፡፡ ከሁሉም በፊት ተማሪዎች የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው መረዳት ይችሉ ዘንድ፣ በክፍል ውስጥ በቂ ልምምድ ማድረግ አለባቸው፡፡ የመምህሩ ሚና ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ድጋፍ መስጠት ማንበባቸውን መከታተል፣ የክፍሉን ሁኔታ መቆጣጠር ነው (silberstein: 1987:32)::

ይሁን እንጂ በምልከታው ማረጋገጥ እንደተቻለው የመምህራን ሚና በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ በምልከታው የታቀፉት መምህራን በሙሉ በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለተማሪዎቻቸው ያነባሉ፡፡ ከመምህራኑ ውስጥ 20% ያህሉ ምንባቡን ዓረፍተ ነገር በዓረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በአንቀጽ ማብራሪያ እየሰጡ ያነቡታል፡፡ ስለሆነም መምህራን የሚያከናውኑት ተማሪዎች ሊያከናውኑት የሚገባውን ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ተማሪዎች አንድ ለትምህርት የቀረበ ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ በፀጥታ ቢሆን እንደሚሻል የመስኩ ባለ ሙያዎች (Greenwood 1981:82) ያስገነዝባሉ፡፡ በገሀዱ ዓለም የዕለት ተዕለት ሕይወታችን የምናነበው በፀጥታ ከመሆኑም ባሻገር፣ በተለይም ጽሑፍ የሚነበብበት ዓላማ መልዕክቱን ለመረዳት ከሆነ መነበብ ያለበት በፀጥታ ነው (Getachew 1996:26፣ Molla 1987፣5፣ Lewis እና Jimmie 1985:111፣Nuttall 1982:21)::

በዚህ ጥናት ማረጋገጥ እንደተቻለው ግን አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች እንዲያነቡ በሚደረግበት ጊዜ የሚያነቡት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ነው፡፡ በምልከታው ከታቀፉት መምህራን ውስጥ ተማሪዎቻቸውን ተራ በተራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ የሚያደርጉት 43.75 ሲሆኑ፣ ተማሪዎቹ ምንባቦቹን በፀጥታ እንዲያነቡ የሚያደርጉ

መምህራን ግን 20% ናቸው። ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜም ፊደላትንና ቃላትን ሲገድፉ ወይም አሳስተው ሲያነቡ መምህሩ ንባባቸውን በማቋረጥ ራሱ አስተካክሎ ያነበዋል፤ ወይም ተማሪዎቹ እንደገና አስተካክለው እንዲያነቡ ያደርጋል። እንደ ጥናቱ አቅራቢ እምነት፣ አንባቢው ተማሪ በሚሳሳትበት ጊዜ በተደጋጋሚ በዚህ መንገድ ለማስተካከል መሞከር አንባቢው "አሁን ምን እሳሳት ይሆን?" እያለ እንዲጨነቅ ሊያደርገው ይችላል። ይህም ጽሑፉን የመረዳት አቅሙን ይገድብበታል።

አንድ ለትምህርት የቀረበ ምንባብ ከተነበበ በኃላ የሚከናወኑት ተግባራት ተማሪዎች ምንባቡን የበለጠ እንዲረዱት የሚያስችሉ ሊሆኑ ይገባል። ከምንባቡ በኃላ የሚቀርቡት ጥያቄዎችና ውይይቶች ዋነኛ ዓላማው አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር ነው። (Greenwood፣1981:83፣ Nuttall 1982)። በተለይም ምንባቡ ከተነበበ በኃላ ተማሪዎቹ በጥንድ ወይም በቡድን ውይይት ቢያካሂዱ ምንባቡን የበለጠ ይረዱታል። ይህ አለመደረጉ ግን ከምልከታው ማወቅ ተችሏል። አብዛኞቹ መምህራን ተማሪዎቹ ስለ ተነበበው ምንባብ እንዲወያዩ አያደርጉም። አብዛኞቹ መምህራን ምንባቡ ተነቦ እንዳበቃ በቀጥታ በመጽሐፍ ውስጥ ወደሚገኙት መልመጃዎች ይሸጋገራሉ።

በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ምንባቦችም ሆኑ መልመጃዎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ብቃት ዝቅተኛ እንደሆነ መጠይቁን ሞልተው የመለሱት መምህራን ገልፀዋል። ምንባቦቹ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት አያነሳሱም፤ የተደጋጋሚ ባሕሪ ስላላቸው ለማንበብ ያሰለቻሉ፣ ወዘተ. የሚሉት በመምህራን ከተሰጡት መልሶች መካከል በአብነት የሚጠቀሱ ናቸው። በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ስለሚገኙት ምንባቦችና መልመጃዎች መምህራኑ እነዚህንና የመሳሰሉትን መልሶችና አስተያየቶች ይስጡ እንጂ በምልከታ የታቀፉት መምህራን ከመማሪያ መጽሐፍ ውጭ ሌሎች ምንባቦችን የራሳቸውን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች እንደሚያቀርቡ ታይቷል።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ነው። የሚለውን አስተያየት ምን ያህል እውነት እንደሆነ ለማረጋገጥ የተካሄደ ነው። ለዚህም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በናሙናነት ከተመረጡት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማሰስ ተሞክሯል። በናሙናነት ከተመረጡት ተማሪዎች ውስጥ አብዛኞቹ በተሰጡት አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ያገኙት ውጤት ዝቅተኛ ነው። ስለሆነም በጥናቱ የተካተቱት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ከጥናቱ ውጤት ለመረዳት ተችሏል።

የአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዓላማዎች ተነድፈውለት በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርትነት በመስጠት ላይ እንደሚገኝ በዚህ ሥራ መግቢያ (1.1) ውስጥ ተጠቅሷል። በአጠቃላይ ዓላማዎች ውስጥ አንዱ የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ማዳበር የሚለው ነው። በንባብ ክሂል ከሚካተቱት ውስጥ አንደኛው ደግሞ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር ነው። በጥናቱ የተካተቱት ተማሪዎች በተሰጧቸው አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች ዝቅተኛ ውጤቶች ማግኘትም ይህ ዓላማ ከግብ እንዳልደርስ ያሳያል።

የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ እንዲሆን ከሚያደርጉት ነጥቦች ውስጥ የመማሪያ መጽሐፍ እና በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የንባብ ትምህርት በዋነኛነት ይጠቀሳል። ስለሆነም የመማሪያ መጽሐፉን ብቃት በመመልከት በመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ተሰራጭቷል። በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የንባብ ትምህርትም እንዴት እንደሚከናወን ለማሰስም ከተሰራጨው የጽሑፍ መጠይቅ በተጨማሪ የክፍል ውስጥ ምልከታ ተካሂዷል። ከጽሑፍ መጠይቁም ሆነ ከምልከታው ማረጋገጥ እንደተቻለው የመማሪያ መጽሐፍ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ብቃት የለውም። በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የንባብ ትምህርትም ቢሆን የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበር የሚያስችል አይመስልም። በትምህርቱ ወቅት አብዛኞቹ ተግባራት የሚከናወኑት በተማሪዎቹ ሳይሆን በመምህሩ ነው። ብዙ ጊዜ በክፍል ውስጥ ለትምህርት የቀረበውንም ምንባብ መምህሩ ሲያነብ ተማሪዎች

ያዳምጣሉ። ሁሉም ተማሪዎች እያዳመጡ መሆናቸውን መምህሩ አይከታተልም። ስለሆነም መምህሩ ሲያነብ የተወሰኑ ተማሪዎች ሌሎች ተግባራትን (ለምሳሌ የተለያዩ የቤት ሥራዎችን መሥራት፣ ከጓደኛ መገልበጥ፣ ሌሎች ጽሑፎችን ማንበብ፣ ወዘተ.) እንደሚያከናውኑ በምልከታው ተረጋግጧል።

የመምህሩ ተግባር ለተማሪዎች ድጋፍ መስጠት፣ ችግር ሲገጥማቸው መርዳት፣ የክፍሉን ውስጥ ሁኔታ መቆጣጠር እንጂ፣ በተማሪዎች መከናወን የሚገባቸውን ተግባራት መፈጸም መሆን የለበትም። አብዛኞቹ ተግባራት በተማሪዎች መከናወን ይገባቸዋል። ይሁን እንጂ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንባብ ልምምድ ውስን ነው። ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚቀርቡትን ምንባቦች እንዲያነቡ የሚደረገው አልፎ አልፎ ነው። አልፎ አልፎ በሚያነቡበት ጊዜም ፊደላትን የመግደፍ፣ ቃላትን አሳስቶ የማንበብ፣ የሚጠብቀውን የማላላት ወይም የሚላላውን የማጥበቅ እና የመሳሰሉትን ስሕተቶች ሲፈጽሙ መምህሩ ጣልቃ እየገቡ ያስተካክላቸዋል ወይም እንደገና አስተካክለው እንዲያነቡ ይነግራቸዋል። ይህም ተማሪዎቹ የጽሑፍን መልዕክት ለመረዳት ከማተኮር ይልቅ ተሳሳትኩ አልተሳሳትኩ እያሉ እንዲጨነቁ ያደርጋቸዋል። ጭንቀታቸው ትኩረታቸውን ይበትንባቸዋል፤ ሊኮተኮት የሚገባውን የማስተዋል ችሎታ ያጠወልገዋል።

ከዚህ ጥናት መረዳት እንደተቻለው በክፍል ውስጥ ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ በአብዛኛው ተግባራዊ የሚሆነው በፀጥታ ከማንበብ ይልቅ ድምፅን ከፍ አድርጎ የማንበብ ስልት ነው። እንደ አስፈላጊነቱ ሁለቱንም ተግባራዊ ማድረግ ቢቻልም ብዙ ጊዜ መበረታታት ያለበት የፀጥታ ንባብ መሆን እንደሚገባው የመስኩ ባለሙያዎች ያስገነዝባሉ። ይህም በሀገራችን በአማርኛ ቋንቋ ንባብን በማስተማር ሂደት ጥናት ሊካሄድበት የሚገባ ቢሆንም፣ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በማስነበብ ላይ ብቻ የሙጥኝ ማለት የለባቸውም። ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ በዝምታ በማንበብ መረዳት ይችሉ ዘንድ በቂ ልምምድ ማድረግ ይገባቸዋል።

በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦችም ሆነ መልመጃዎች የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ የማዳበር ብቃታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉት መምህራን ገልፀዋል። ይሁን እንጅ በናሙናነት የተመረጡት መምህራን ከመጽሐፍ ውጭ ይሻላሉ የሚሏቸውን ሌሎች ምንባቦች ለትምህርት እንደማያቀርቡ፣የራሳቸውን አንብቦ የመረዳት መልመጃዎችም እንደ ማይሰጡ

በምልከታው ተረጋግጧል። በናሙናነት ተመርጠው ሲያስተምሩ ምልከታ የተካሄደባቸው መምህራን የሚያስተምሩት በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ብቻ በመመሥረት ነው። መጽሐፉ ብቃት እንደሌለው እስካመኑ፣ ምንባቦቹና መልመጃዎቹም የተማሪዎችን ፍላጎት አያነሳሱም፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታን የማዳበር ብቃታቸውም ዝቅተኛ ነው። እስካሉ ድረስ ሌሎች ብቁ ናቸው፣ የተማሪዎችን ፍላጎት ያነሳሳሉ፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታንም ያዳብራሉ የሚሏቸውን ጽሑፎች እያሰባሰቡ ለትምህርት ማቅረብ ይጠበቅባቸው ነበር።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትንና የመሳሰሉትን ሁሉ በአንድነት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲገኝ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናሉ።

## 5.2 አስተያየት

የጥናቱ አቅራቢ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ በማለት የሚከተሉትን አስተያየቶች ይሰነዝራል፤

ሀ. በክፍል ውስጥ በሚደረገው የንባብ ትምህርት ተማሪዎች ሙሉ ተሳትፎና በቂ ልምምድ ማድረግ አለባቸው።

ለ. መምህራኑ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ብቻ ከመመካት ይልቅ የተለያዩ ምንባቦችን በማሰባሰብ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

ሐ. መምህራኑ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ንባብን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ሥልጠና ሊሰጣቸው ይገባል።

መ. በፀጥታና እና ድምፅን ከፍ አድርጎ የማንበብ ጠቀሜታ በክፍል ውስጥ በምን መልክ መቀናጀት እንዳለባቸው በሌሎች አጥኝዎች ቀጣይ ጥናት ሊካሄድ ይገባል።

ሠ. የተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚያስችል የማስተማር ዘዴ በተመራማሪዎች ተጠንቶ ቢቀርብ ችግሩ ሊቃለል ይችላል።

# ዋቢ ምንጮች


Bright, J. McGregor, 1981. *Teaching English as Second Language* Harlow: Longman.

Celce- Murcia, M. (ed) 1991. *Teaching English as a Second or Foreign Language.* (2nd ed). Bosten: Hicinle and Hicinle Publisher Ltd.

Davey, Beth 1987, *Relations between Word Knowledge and Comprehension, Generalization across Tasks and Readers.* Journal of Educational Research, 80(3)pp179-183

David, A. 2005. *Reading Skills in English.* Delhi: Commonwealth Publishers.

Davies, F. 1995. *Introducing Reading.* London: Pengiuirn Group.

Fry, E. 1963. *Reading faster.* A drill book. Cambridge university press.

Gage, N.C. 1963. *Handbook of research on teaching.* Chicago: Rand Mc Nally and Co.

Getachew Astrate.1996. "*The Teaching of Reading in Government High Schools in A.A Diseriptwe Study.*" Unpublished M.A theses, Addis Ababa University.

Grant, N.1987. *Making Most Out of your Textbook.* New York: Longman.

Greenwood, J. 1981. "Comprehension and Reading" in Abbott, G. and Wingard, P. (eds) *Teaching of English as an International Language: A Practical Guide.* Oxford: Oxford University Press.

Grellet, F. 1981. *Developing Reading Skills: A Practical Guide to Reading Comprehensive Exercises.* Cambridge: Cambridge University Press.

Harmer. J. 1991. *The Practice of English Language Teaching.* Cambridge: Cambridge Person Educational.

Harris, A. and Sipay, E. 1990. *How to Increase Reading Ability: A Guide to Developmental and Remedial Methods.* London: Longman Group Ltd.

Harris, A.J. 1965. *How to increase reading ability.* New York: David and McKay Company.

Hughes, A. 1995. *Testing for Language Teachers.* Cambridge University Press.

Johnson, P.1982. "Effects on Reading Comprehension of Building Background Knowledge." *TESOL Quarterly* 16:4, 503-516

Kavale, K. 1979. *"Selecting and evaluating reading tests."* In Reading tests and teachers: A practical guide. R. Schreir (ed.), pp. 9-32.

Lewis, M 1985. *Practical Guides for Language Teaching.* London: Language Teaching Publications.

Lindsay 2006. *Learning and Teaching English.* Oxford: Oxford University Press.

Madson, H.S. 1983. *"Coping with English Language Transition Problems at secondary and university levels."* HSIU, (Memographed).

Masson, H.S. 1970. *Techniques in Testing.* Oxford Printing Press.

McDonough, J. and Ch. Shaw (1993). *Materials and Methods in ELT.* Cambridge: Blach well publisher Ltd.

------------- 2003. *Materials and Methods in ELT.* Oxford: Oxford University Press.

Mei-yun, Yue. 1997. "Teaching Efficient EF2" in karal, T. (ed.). *Teacher Development: Making the Right Moves.* Washington, D.C.: United States Information Agency.

Molla Jembere. 1987. "*Addis Ababa University Freshman Students Reading Speed in English Language*" Unpublished M.A thesis, Addis Ababa University.

Narayanaswamy, K.R. 1975. *"The Measurement of reading ability."* Jounral of English Language Teaching, 29 (2), pp. 143-150.

Nuttall, C. 1982. *Teaching Reading Skills in a Foreign Language.* London: Heinemann Educational Books Ltd.

-------------2000. *Teaching Reading Skills for in a Foreign Language.* London: Heinemann Educational books.

Sheng, H. J. 2000. "A Cognitive Model for Teaching Reading Comprehension" *The English Teaching Forum.* Vo.38 Mum.4 pp12-15

Silberstein, S. 1987. *"Let's take an other look at reading:* Twenty- Five Years of reading instruction. Forum, 25(4), pp. 784-786.

Smith, F. 1985. *Reading.* Cambridge: Cambridge University Press

Spapalia, Anthony 1987. "Interaction of Reader and Text" in Rivers, W.M.(ed). *Interactive Language Teaching.* Cambridge: Cambridge University Press.

Statman, S. 1981. "*The Activation of a Systematic Theory*: a Pedagogical Theory in the EFL Classroom" Journal of English language teaching 35(3), PP. 232-233

Stavans, A, 1993 "*Assessing EFL reading comprehension*: The cause of system Ethiopian learners", 21 (4) PP. 481-491

Ur, P. 1996. *A Course in Language Teaching: Practice and Theory.* Cambridge: Cambridge University Press.

Wallace, C. 1992. *Reading.* Oxford: Oxford University Press.

Weir , C.J. 1990. *Communicative Language Testing.* New York: Prentice Hall.

Williams, E. 1990. *Reading in the Classroom.* London: McMillan publishers, Ltd.

ሳቀው ደምሴ በ1991 ዓ.ም:: በተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ፣ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ግምገማ M.A.

ማስተዋል ውበቱ 1989 :: የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በአዲስ አበባ በሚገኙ 4 ከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት። M.A.

በየነ ማሞ 1985። *"በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የቋንቋውን ክሂሎች የሚያዳብሩ ናቸው።"* ለአማርኛ ማስተማር ማስትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ (ያልታተመ)።

ተስፋዬ ሸዋዬ (1981)። *"ስነልሳንና ቋንቋን ማስተማር"* አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)።

ተሾመ ፎርሲቶ 1997። በአላባ ጠንባሮ ዞን የሚገኙ የ2ኛ ደረጃ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውንና የማንበብ ፍላጎታቸው። M.A.

ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1984። *የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ ከ9- 12 ክፍል።* አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድርጅት።

# አባሪዎች

## ለመምህራን የተሰራጨ የጽሑፍ መጠይቅ

## በሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ

ይህ የጽሑፍ መጠይቅ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጥናት የተዘጋጀ ነው፡፡ ጥናቱ የታለመውን ግብ ሊመታ የሚችለውም ትክክለኛ መረጃ ማሰባሰብ ሲቻል ነው፡፡ ስለሆነም መጠይቁን በጥንቃቄ ይሞሉ ዘንድ በትህትና እየጠየቅሁ ለትብብርዎ አመሰግናለሁ፡፡

### ክፍል አንድ አጠቃላይ መረጃዎች

ከዚህ በታች ያሉትን ባዶ ቦታዎች ትክክለኛ መረጃዎችን ይሞሉልኝ ዘንድ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

1. ጾታ----------
2. የትምህርት ደረጃ ----------------------
3. የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት-----
4. የአገልግሎት ዘመን--------------------
5. አሁን የሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት------------------------------
6. የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ-------

### ክፍል ሁለት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች መካከል የሚስማሙበትን ምርጫ የሚያመላክተውን ሆሄ እየመረጡ በመክበብ ያመልክቱ፡፡

1. በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚከተሉት ውስጥ ይበልጥ የሚያጐለብተው የትኛውን ነው

   ሀ. አንብቦ የመረዳት ችሎታን ሐ. ሐሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታን

   ለ. አዳምጦ የመረዳት ችሎታን መ. ሐሳብን በንግግር የመግለጽ ችሎታን

2. በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የሚቀርበው ትምህርት ይበልጥ የሚያተኩረው በየትኛው ክሂል ላይ ነው፡፡

   ሀ. በማዳመጥ ለ.በመናገር ሐ. በማንበብ መ. በመጻፍ

3. ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች መልመጃዎችን ምን ያህል ይሰጣሉ

   ሀ. ሁልጊዜ እሰጣለሁ ሐ. አብዛኛውን ጊዜ እሰጣለሁ

   ለ. አልፎ አልፎ እሰጣለሁ መ. እንዲሁ አልፈዋለሁ

4. በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት መልመጃዎች ከሚከተሉት ውስጥ ይበልጥ የሚያተኩሩት በየትኛው ላይ ነው

ሀ. አንብቦ መረዳት ሐ. ሀሳብን በንግግር በመግለጽ

ለ. አዳምጦ በመረዳት መ. ሀሳብን በጽሑፍ በመግለጽ

5. ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ውስጥ በየጊዜው የሚሰጧቸውን መልመጃዎች የሚሰሩ ምን ያህል ናቸው

ሀ. ሁሉም ይሰራሉ ሐ. አብዛኞቹ ይሰራሉ

ለ. ጥቂቶቹ ይሰራሉ መ. ጨርሶ አይሠሩም

6. ለተማሪዎች የሚሰጧቸውን መልመጃዎች ምን ያህል ተከታትለው ያርማሉ

ሀ. ሁልጊዜ አርማለሁ ሐ. አልፎ አልፎ አርማለሁ

ለ. አብዛኛውን ጊዜ አርማለሁ መ. ጨርሶ አላርምም

7. ተማሪዎች ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ የሚደረገው

ሀ. ሁልጊዜ ነው ሐ. አልፎ አልፎ ነው

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው መ. በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ አይደረግም

8. ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ካሉት ውጭ ሌላ ተጨማሪ ምንባቦችን የሚያነቡት

ሀ. ሁልጊዜ ነው ሐ. አልፎ አልፎ ነው

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው መ. ተጨማሪ ምንባቦችን አያነቡም

9. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በየተራ እንዲያነቡ የሚደርገው

ሀ. ሁልጊዜ ነው ሐ. አልፎ አልፎ ነው

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ነው መ. ድምፃቸው ከፍ አድርገው እንዲያነቡ አይደረግም

10. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለትምህርት የሚቀርቡትን ምንባቦች በየተራ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ የሚያደርጉት ከሆነ በሚያነቡበት ጊዜ ቢሳሳቱ ምን እርምጃ ይወስዳሉ

ሀ. የንባብ ሂደቱን በማቋረጥ ስህተቱን እራሴ አስተካክዬ አነባለሁ

ለ. መሳሳታቸውን ያላወቅሁ በመምሰል ንባባቸውን እንዲቀጥሉ አደርጋለሁ

ሐ. አስተካክለው እስከሚያነቡት ድረስ የተሳሳቱትን እንዲደግሙት አደርጋለሁ

ክፍል ሶስት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ሐሳቦችና ጥያቄዎች አምስት አምስት መመዘኛዎች ተሰጥተዋል። በየሐሳቦቹና ጥያቄዎቹ ከተሰጡት መመዘኛዎች ውስጥ በሚስማሙበት መመዘኛ ስር የ"✓" ምልክት ያድርጉ

5. በጣም ከፍተኛ 3. መካከለኛ 1. በጣም ዝቅተኛ

4. ከፍተኛ 2. ዝቅተኛ

| ተ.ቁ | ሐሳብ ጥያቄ | መመዘኛ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ብቃት፣ | | | | | |
| 2 | ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የመስራት ፍላጎት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 3 | ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 4 | ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት የንባብ ልምምድ | | | | | |
| 5 | በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚጫወተው ሚና? | | | | | |
| 6 | የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ውስጥ በክፍል ውስጥ የማንበብ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ብዛት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 7 | ተማሪዎች በአማርኛ የተጻፈ የተለያዩ ጽሑፎችን የማንበብ ፍላጎት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 8 | ተማሪዎች አንድን ምንባብ ከአነበቡ በኃላ የሚሰጡት ምላሽ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 9 | ከክሂሎች አንጻር ምንባብን ለማንበብ የሚሰጡት ጊዜ ምን ያህል ነው | | | | | |
| 10 | ተማሪዎች በምናይበት ጊዜ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው? | | | | | |

ክፍል አራት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሶችዎንና አስተያየቶችዎን በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ላይ ይጻፍ?

1. የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን አያዳብርም የሚሉ ከሆነ ምክንያትዎን ይጻፍ

   ሀ. ------------------------------------ ሐ. ------------------------------------

   ለ. ------------------------------------ መ.------------------------------------

2. የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ነው የሚሉ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል

   ሀ. ------------------------------------ ሐ. ------------------------------------

   ለ. ------------------------------------ መ.------------------------------------

3. የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ምን መደረግ አለበት ይላሉ

   ሀ. ------------------------------------ ሐ. ------------------------------------

   ለ. ------------------------------------ መ.------------------------------------

የምልከታ ዝርዝር (Observation sheet)

**በ9ኛ ክፍል ውስጥ በሚካሄደው የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ላይ ምልከታ (Observation) ለማካሄድ የተዘጋጀ የመከታተያ ዝርዝር**

ትምህርት ቤት ----------------------------------------

መምህር ---------------------------------

| ተ.ቁ | የመምህሩና የተማሪዎች ተግባራት | ት1 | ት2 |
|---|---|---|---|
| 1 | መምህሩ የምንባቡን ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጽፋል | | |
| 2 | መምህሩ የምንባቡን ርዕስ ለተማሪዎች በቃል ይናገራል | | |
| 3 | መምህሩ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ እዳዲስ ቃላትን ፍችዎች ለተማሪዎች ይገልጻል | | |
| 4 | መምህሩ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ አዳዲስ ቃላትን በጥቁር ሰልዳው ላይ ይጽፋል | | |
| 5 | መምህሩ ለተማሪዎች ምንባቡን የሚያነቡበትን ዓላማ ይገልጽባቸዋል | | |
| 6 | ተማሪዎች ስለምንባቡ መልዕክት ሐሳብ ይሰነዝራሉ | | |
| 7 | ተማሪዎች በፀጥታ ያነባሉ | | |
| 8 | መምህሩ ምንባቡን ድምፁን ከፍ አድርጐ ያለምንም ገለጻ ያነባል | | |
| 9 | መምህሩ ድምፅን ከፍ አድርጐ ዓረፍተ ነገር በዓረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ በአንቀጽ እያብራራ ያነባል | | |
| 10 | ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተራ በተራ ያነባሉ | | |
| 11 | ተማሪዎች ስለተነበበው ምንባብ በጥንድ ወይም በቡድን እርስ በርስ ይወያያሉ፡፡ | | |
| 12 | መምህሩ የምንባቡን ፍሬ ሐሳብ ለተማሪዎች ይገልጻል | | |
| 13 | መምህሩ ተማሪዎችን የራሱን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቃል | | |
| 14 | ተማሪዎች ግልጽ ያልሆነላቸውን ነጥብ መምህሩን ይጠይቃሉ | | |
| 15 | ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቡበት ጊዜ ሲሳሳቱ<br>15.1 መምህሩ ንባባቸው በማቋረጥ ስህተቱን አስተካክሎ ያነበዋል<br>15.2 አንባቢው ተማሪ ማንበቡን አቅርጦ እንዲያስተካክል በመምህሩ ይነገረዋል<br>15.3 ተማሪው ማንም ጣልቃ ሳይገባበት ማንበቡን ይቀንሳል | | |

# አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች

## ሀ. ፈተና አንድ

ስም ከነአባት ----------------------------------------------

ፆታ ------------------

ዕድሜ ---------------------

**አጠቃላይ መግለጫ፡-** የዚህ ፈተና ዋነኛ ዓላማ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማጥናት ነው፡፡ በመሆኑም ምንባቡን በተቻለ መጠን በጥንቃቄና በተለመደው ፍጥነት ከነበብክ/ሽ/ በኋላ ከምንባቡ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች በተሰጡት መመሪያዎች መሠረት መልስ/ሺ/፡፡

### ምንባብ አንድ

### ቋንቋና ጽሕፈት

የሰው ልጅ አሁን የምናውቀውንና የምንሠራበትን ቋንቋ ከመፍጠሩ በፊት ብዙ ሚሊዩን ዓመታት በልዩ ልዩ ዘዴዎች በመግባባት ሲጠቀም ቆይቷል፡፡ ከነዚህ ልዩ ልዩ ዘዴዎች አንዱ ምልክት በመስጠት መግባባት ነበር፡፡ በእንደዚህ ያለ ሁናቴ ብዙ ሺህ ዓመታት ካሳለፈ በኃላ ቀስ በቀስ በድምፃዊ ቋንቋ ወደ መግባባት ደረጃ ደረሰ፡፡ በየጊዜው ከሚያገኛቸው ልምዶች ይበልጥ ወደ ተራቀቀ ደረጃ ለመድረስ ሲጣጣር ከቆየ በኃላ ለአንዳንድ ግዙፍ ነገሮች በድምፅ ኅብረት ስያሜ ከመስጠት አልፎ ረቂቂ ለሆኑ ነገሮች መጠሪያና መግባቢያ ዘዴ ወደ መፍጠሩ ደረጃ ደረሰ፡፡ በስልጣኔው እጅግ እየተራመደና በአስተሳሰቡ በጣም እየተራቀቀ ሲሄድ በቋንቋው ጥበብና ሳይንስ ሥርዓትም እጅግ ከተራቀቀ ደረጃ ደርሷል፡፡ እንግዲህ የሰው ልጅ የቋንቋ እድገት ከስልጣኔው እድገት ጋር አብሮ የሚራመድ ሂደት መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

ቋንቋ ከምልክታዊ መግባቢያነት ወደ ድምፃዊ መግባቢያነት በመሻጋገሩ የሰው ልጅ አሌ የማይባል እድገት ቢያሳዩም ወደ መጨረሻው የመገናኛ ዘዴው እድገት ደረጃ እንዳልደረሰ ይሰማው ነበር፡፡ ከቋንቋው ውጭ የሆነና ለቋንቋ አጋዥ የሆነ ሌላ መገናኛ ዘዴ እንደሚያስፈልገው በየጊዜው በሚያደርጋቸው ሙከራዎች ይገልጽ ነበር፡፡ እነዚህም በደንጊያ፣ በብረት፣ በቆዳ፣ በእንጨትና ነበሩ፡፡ ወገኑ በሞተበት ጊዜ ሞላላ ድንጊያ እመቃብሩ ላይ ማድረጉ በዚያ ቦታ ሰው መቀበሩን ለሌሎች መልዕክት ለማስተላለፍ ነው ይህም ያንን ቦታ በአካባቢው ካሉት ቦታዎች የተለየ ስለሚያደርገው መልዕክት

በሚገባ ተላልፏል ማለት ነው እንዲህ ያለው የምልክት መግባቢያ በጣም አስፈላጊ የሆነበት ለጊዜና ለቦታ ችግር መፍትሄ ለመስጠት ነው።

ከቦታ ርቀት አንፃር ስናየው በቋንቋው የሚደረገው ግንኙነት ውሱን ሆኖ እናገኘዋለን። በቋንቋ ግንኙነት የሚያደርጉት በአካል አንድ ቦታ መገኘት አለባቸው ለጽሕፈት ግንኙነት ግን ይህ አስፈላጊ አይደለም ለምሳሌ ያህል በሠለጠነው ዓለም ዘንድ መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ ብትን ጽሑፎች፣ ደብዳቤዎች ምን ያህል ሰውን ከሰው ሕዝብን ከሕዝብ፣ ዘመንን ከዘመን የማገናኘት ችሎታ እንዳላቸው መገመቱ ብቻ ይበቃል። ሌላው ሕዝብ የደረሰባትን የሥልጣኔ ደረጃ የምርምሩንና የድካሙን ውጤት ብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር ሳንጓዝና እዚያው ቦታ በአካል ሳንገናኝ ካላንበት ሆነን አንብበን መረዳትና የድካሙ ፍሬ ተካፋዮች መሆን እንችላለን።

በዚህ አንፃር ደግሞ ስናየው ጽሕፈት በአንድ ዘመን የተሠራውን የሰውን ልጅ የሥልጣኔ ፍሬ ባለንበት ዘመን እንድንጠቀምበት ይረዳናል። ከዚህም በላይ ያለፈውን ለአሁኑ ትውልድና የዛሬውን ለመጭው ትውልድ ማስተላለፍ ይቻላል። በአገራችን "በቃል ያለ ይረሳል በጽሑፍ ያለ ይወረሳል" እንደሚባለው ጽሕፈት፣ ግለሰብም ሆነ ኅብረተሰብ የሠራውንና እስቦ የደረሰበትን የስልጣኔውን ቅርጽ ለሚመጣው ትውልድ ማስተላለፊያ፣ ካለፈውም ትውልድ መቀበያ ዋና ዘዴ ነው፣ በእርግጥ የሰው ልጅ ታሪክ፣ ያለፈው ትውልድ ዜና፣ ባህልና ወግ ያለ ጽሕፈትም ሊተላለፍ ይችላል። ይሁንና እንደዚህ ባለው መንገድ የሚተላለፈው እውቀት ሳይቀነስበትና ሳይጨመርበት ጥራት ባለው ሁኔታ ይተላለፋል ማለት የሚያስተማምን አይደለም። ጊዜውም እጅግ እየራቀ ሲሄድ ደብዛው ጠፍቶ ሊቀር ይችላል። ሊደርሰን የሚችል ነገርም ቢኖር ፈጽሞ ሌላ መልክ ይዞና ከእውነት የራቀ አፈ ታሪክ ሆኖ ነው። ሌላውም ይቅርና ጽሕፈት ስለ ሌላቸውም ሕዝቦች እውነተኛ ታሪክ ለማወቅ የበቃነው ጽሕፈት የነበራቸው ጐረቤቶቻቸው ስለእነሱ ስለጻፍልን ብቻ ነው።

*መመሪያ አንድ፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥ በምንባቡ መሠረት መልስ የሚሆነውን ምርጫ የሚያመለክተው ሆሄ በመክበብ አመልክት (አመልክች)*

1 --- የስልጣኔ ፍሬ ------- የሚለው ሐረግ --------- ማለት ነው።

ሀ. የእድገት ግኝት ሐ. የብልጽግና ውጤት

ለ. የእድገት ውጤት መ. ሀ ና ለ

2. አሁን የምንጠቀምበት ቋንቋ ከመፈጠሩ በፊት ሰዎች --------- ይግባቡ ነበር፡፡

ሀ. በምልክት ለ. በንግግር ሐ. በጽሕፈት መ. በሁሉም

3. ከሚከተሉት መካከል አንዱ የጽሕፈት አገልግሎት አይደለም

ሀ. በቦታ መወሰንን አይጠይቀመ

ለ. ሥልጣኔን ከትውልድ ትውልድ ለማስተላለፍ አይጠቅምም

ሐ. በጊዜ መወሰንን አይጠይቅም

መ. መልሱ አልተሰጠም

4. በቋንቋ የሚደረገው ግንኙነት ውስን የማይሆነው

ሀ. ከጊዜ አንጻር ነው ለ. ከጊዜና ከቦታ አንጻር ነው

ሐ. ከቦታ አንጻር ነው መ. ሐሳብን ከመግለጽ አንጻር ነው

5. በቋንቋ የሚደረገው ግንኙነት ውስን የሚሆነው

ሀ. ከጊዜ አንጻር ነው ለ. ሐሳብን ከመግለጽ አንጻር ነው

ሐ. ከቦታ አንጻር ነው መ. ሀ እና ለ ትክክል ናቸው

*መመሪያ ሁለት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልስ/ሽ*

1. የቋንቋና የጽሕፈት በሚለው ምንባብ ቀዳሚውን በቅደም ተከተል ጻፍ/ፊ/

ሀ ---------------------- ለ. ---------------------- ሐ. ---------------------

2. በምንባቡ መሠረት ቋንቋ ማለት ምን ማለት ነው

ሀ ---------------------- ለ. ---------------------- ሐ. ---------------------

3. በምንባቡ ውስጥ ስንት ዓይነት የመግባቢያ ዘዴዎች ተጠቅሰዋል -----------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

4. አንቀጽ ሶስት ስለምን ይገልጻል

5. የሰው ልጅ የቋንቋ እድገት ከስልጣኔው ዕድገት ጋር አብሮ የሚራመድ ሂደት ነው ሲል ምን ማለቱ ነው ------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

ለ. ፈተና ሁለት

ስም ከነአባት -------------------------------

ፆታ ------

ዕድሜ -------

**አጠቃላይ መግለጫ፡-** የዚህ ፈተና ዋነኛ ዓላማ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማጥናት ነው፡፡ በመሆኑም ምንባቡን በተቻለ መጠን በጥንቃቄና በተለመደው ፍጥነት ካነበብክ /ካነበሽ/ በኋላ ከምንባቡ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች በተሰጡት መመሪያዎች መሠረት መልስ/ሽ/ ፡፡

## ምንባብ

ለሰው ልጅ ሕልውና ማቆያና ማረጋገጫ እንዲሁም ለመሠረታዊ ፍላጐቱ ማሟያ መሠረቱ ሥነ ነው፡፡ ከኃላ ቀርነት ዳዴ ቆሞ ለመሄድ የሚችለው ባለመቋረጥ በሚያከናውነው የሥራ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ፍላጐቱን ለማሟላት በሚያደርገው የዘወትር የሥራ እንቅስቃሴ የአስተሳሰብ ብስለቱ እየዳበረና እየሰላ በመምጣት የፈጠራ ችሎታው ያድጋል፡፡

የሥራ ሁሉ ፍሬውን ስለማያይ የመንፈስ እርካታ ቢያገኝም ፍላጐቱን ሊገታ ስለማይችል የሥራ እንቅስቃሴውን ያለማቋረጥ ይቀጥላል፡፡ ለሰው ልጅ መሻሻልና ዕድገት እጅግ ጠቃሚ የሆኑት ሳይንስና ቴክኖሎጂ አሁን ካሉበት ደረጃ የደረሱት ያለማሳለስ በተደረገው ምርምር ነው፡፡ "ፍላጐት የመፍጠር እናት ናት" እንደሚባለው መሥራት ከፍላጐት ይመነጫል፡፡ ፍላጐት ደግሞ በተጨባጭ ተግባራዊ ሲሆን እምቡጡ አሽቶ ፍሬ ይሆናል፡፡

ስላለፉት ዘመናት ወደ ኃላ መለስ ብለን ስናሰላስል ያለ ሥራ የተገኘ አንድም ውጤት የለም፡፡ የሰው ልጆች ከምንም ተነስተው ፍላጐታቸውን ለማሟላት ባደረጉት የሥራ መፍጨርጨር በስልጣኔ እይፉፉ በመምጣት በዓለም ውስጥ የሚገኘውን ሀብት በጥቅም ላይ እያዋሉ ናቸው፡፡ ዛሬ በምድርና በሕዋው ውስጥ የሚደረገው ምርምር ያለእፎይታ ስለቀጠለ ከአሁን በፊት ያልታዩ ግኝቶች በየእለቱ እየበዙ በመምጣት ላይ ናቸው፡፡

1. በምንባቡ መሠረት የሠራ የመንፈስ እርካታ የሚገኘው፤

   ሀ. ፍላጐቱን ሊገታ ስለማይችል ለ. ፍሬውን ስለሚያዩ

   ለ. የሥራ እንቅስቃሴው ስለሚቀጥል መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

2. የሰው ልጆች በዓለም የሚገኘውን ሀብት ሊጠቀሙበት የቻሉት በምንድ ነው?

   ሀ. የኃላ ታሪካቸውን ስላስታወሱ ነው፡፡

ለ. ለመኖር መሥራት አስፈላጊ መሆኑን ስለተረዱ ነው፣

ሐ. ከምንም ተነስተው ስለተፍጨረጨሩ ነው።

መ. አዳዲስ ግንኙቶች እፎይታን ስላስገኙላቸው ነው።

3. የኃላ ቀርነት ዳዴ ሲል ምንን ለመግለፅ ነው

ሀ. አዝጋሚ መሆኑን ለ. ፈጣን መሆኑን ሐ. ተራማጅ መሆኑን

መ. ሙት መሆኑን

4. የሰው ልጅ የሥራ እንቅስቃሴ ካደረገ ያድጋል የተባለው ምኑ ነው

ሀ. ፍላጐቱን ለማሟላት የሚያከናውነው ተግባር፣ ለ. የመንፈስ እርካታው

ሐ. የፈጠራ ችሎታ መ. የአስተሳሰብ ብስለቱ ያስከተለው ተግባር

5. "ፍላጐት የመፍጠር እናት ናት" የሚለው አነጋገር ከየትኛው ጋር ይስማማል

ሀ. ሰው የሚፈልገውን ካገኘ መፍጠር ይችላል

ለ. ሰው ለመፍጠር የሚሞክረው ፍላጐት ሲኖረው ነው።

ሐ. እምቡጥ አሽቶ ፍሬ ይሆናል

መ. ፍላጐት ህልውናና ፈጠራ አንድ አካል አንድ አምሳል ናቸው።

መመሪያ ሁለት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ላይ ፃፊ/ፍ

1. በስልጣኔ መፋፋት ማለት ምን ማለት ነው?

--------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

2. ግኙቶች በሚለው ቃል ላይ የተጨመረው ቅጥያ ምንን ያመለክታል?

--------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

3. ከሚከተሉት ውስጥ የምንባቡን ዋና ትኩረት የያዘው ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው?

--------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት ተማሪ ይህ ጥናት የራሴ ሥራና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ጽሑፎች ምንጮች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

ስም ------------------------------

ፊርማ ------------------------------

ቀን ------------------------------

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ